# ዓለም-አቀፉ የአካል ጉዳተኞች መብት ስምምነትና የጤና መብት ጽንሰ-ሀሳብ

ፀሀፊ፡ዘመድኩን ግርማ

ይህ ህትመት በኢትዮጵያ የህግ ባለሙያ አካል ጉዳተኞች ማህበር ከኦፕን ሶሳይቲ ኢኒሼቲብ ፎር ኢስተርን አፍሪካ ጋር በመተባበር የተዘጋጀ ነው። በሰነዱ የተገለጸ ይዘት እና ሀሳብ/አመለካከት በማንኛውም መንገድ የኦፕን ሶሳይቲ ኢኒሼቲብ ፎር ኢስተርን አፍሪካ አመለካከትን አያንጸባርቅም።

Contents

**ክፍል 1. ጠቅላላ** ..... 1

1.1. የሰብአዊ መብቶች ጽንሰ-ሀሳብ ..... 1

1.1.1. የሰብአዊ መብቶች ምንነት ..... 1

1.1.2. የኢኮኖሚ፣ የማህበራዊና የባህል መብቶችና ልዩ ባህሪያቸው ..... 2

1.2 የጤና መብት ጽንሰ-ሀሳብ በዓለም-አቀፍ የሰብአዊ መብቶች ሕግጋት ውስጥ ..... 3

**ክፍል 2. የአካል ጉዳተኞች መብት እንደሰብአዊ መብት ጉዳይ** ..... 8

2.1. የአካል ጉዳተኝነት ብያኔ በዓለም-አቀፉ የአካል ጉዳተኞች መብት ስምምነት ውስጥ ..... 9

2.2. የዓለም-አቀፉ የአካልጉዳተኞች መብት ስምምነት ጠቅላላ መርሆዎች እና ጠቅላላ ግዴታዎች ..... 10

2.2.1. ጠቅላላ መርሆዎች ..... 10

2.2.2. ጠቅላላ ግዴታዎች ..... 10

**ክፍል 3. የጤና መብት በዓለም-አቀፉ የአካል ጉዳተኞች ስምምነት ውስጥ** ..... 13

3.1. እያደገ የሚሄድ ገቢራዊ የማድረግ ግዴታና የመድልኦ አልባነት መርህ ..... 14

3.2. የተደራሽነትና ምቹነት መርሆና የጤና አገልግሎት ..... 15

3.2.1. መድልኦ-አልባነት እና የእኩል ተጠቃሚነት ..... 16

3.2.2. ቁስ-አካላዊ ተደራሽነት (Physical Accessibility) ..... 17

3.2.3. ኢኮኖሚያዊ ተደራሽነት (economic accessibility) ..... 17

3.2.4. የመረጃ ተደራሽነት (information accessibility) ..... 18

3.3. በመረጃ ላይ የተመሰረተ ነጻ ፈቃድ ..... 18

3.4. የፆታና የሥነ ተዋልዶ ጤና አጠባበቅ ..... 19

3.5. የጤና ባለሙያዎችን ግንዛቤ እና እውቀት ስለማዳበር ..... 19

3.6. ወሳኝ የማኅበራዊ ኩነቶች፣ ጤና እና የአካል ጉዳተኞች መብቶች ..... 20

**ክፍል 4 የኢትዮጵያ ሕጎች ከአካል ጉዳተኞች የጤና መብት አኳያ** ..... 21

4.1. የጤና መብት በአካል ጉዳተኞች ስምምነት ውስጥ ያለው ይዘት እና የኢትዮጵያ ሕጎች ..... 21

4.2. መወሰድ ስለሚገባቸው እርምጃዎች ..... 23

## ክፍል 1. ጠቅላላ

የአካል ጉዳተኝነት ብያኔን በተመለከተ ያሉት የግንዛቤ ልዩነቶች እና ለአካልጉዳተኝነት የሚሰጠው ትርጓሜም እንደ አውዱ የሚለያይ መሆኑ በዓለም-አቀፍ ደረጃ በተጨባጭ ያለውን የአካልጉዳተኝነት ስርጭትም ሆነ የአካልጉዳተኞች ትክክለኛ ቁጥር ምን ያክል እንደሆነ ለማወቅ አዳጋች ያደረገው ቢሆንም፣ በዓለም የጤና ድርጅት እ.ኤ.አ. በ2002-2004 በ 59 ሀገራት ውስጥ የተካሄደው የገጽ-ለገጽ የቤት ለቤት የጤና ሁናቴ የዳሰሳ ጥናት እንዳመለከተው፣ በዓለም-አቀፍ ደረጃ 650,000,000 (ስድስት መቶ ሀምሳ ሚሊዮን) አዋቂ ሰዎች አካል ጉዳተኞች እንደሆኑ፤ ከዚህ መካከልም 92,000,000 (ዘጠና ሁለት ሚሊዮን) የሚሆኑቱ ጠንካራ የሚባል የአካል ጉዳተኝነት እንዳለባቸው ግምቱን አስቀምጧል። ይኸው ጥናት ከዚህ በተጨማሪም የአካል ጉዳተኝነት ስርጭቱ በኢኮኖሚያዊ ሁናቴአቸው ዝቅ ባሉ ሀገራት ውስጥ ከፍ እንደሚልና ከጠቅላላ ሕዝባቸው መካከል 18% የሚሆነው ሕዝባቸው አካል ጉዳተኛ እንደሆነ ይህ ደግሞ በኢኮኖሚያዊ ሁናቴአቸው ከፍ ባሉ ሀገራት ውስጥ ካለው ከጠቅላላ ሕዝቡ 11.8% ብቻ ከሆነው ጋር ስናነጻጽረው ከፍ እንደሚል አመላክቷል።

እንዲህ ከፍ ያለ ቁጥር ያላቸው አካል ጉዳተኞች በጠቅላላው በማህበራዊ፣ ኢኮኖሚያዊ፣ ፖሊቲካዊ እንቅስቃሴዎችና ማህበረ-ኢኮኖሚያዊ ተሳትፏቸው የተሟላና ውጤታማ እንዳይሆን መገለልና ተጽእኖዎች ያሉበት ስለመሆኑ ይታወቃል።

### 1.1. የሰብአዊ መብቶች ጽንሰ-ሀሳብ

#### 1.1.1. የሰብአዊ መብቶች ምንነት

ከተለያዩ የዓለም-አቀፍ የሰብአዊ መብቶች ስምምነቶች ይዘት ለመገንዘብ የሚቻለው፣ ሰብአዊ መብቶች በዋነኝነት በሰዎች ልጆች ሰብአዊ ክብር (human dignity) እና ነጻነት (liberty) ላይ እንደሚያተኩሩ ነው። በዚህም ምክንያት ሰብአዊ መብቶች ለሁሉም ሰዎች በእኩል ያለምንም መድሎ በዓለም ሁሉ ውስጥ ላሉ ሰዎች በተፈጥሯዊ ማንነታቸው ብቻ ተፈጻሚ እንደሚሆኑና በመንግስታት ላይም ከፍ ያለ የማክበር፣ የመጠበቅና የማሟላት ግዴታዎችን የሚጥሉ መብቶች ናቸው።

ከዚህ ጋር በተያያዘ፣ በዓለም-አቀፍ ደረጃ፤ ሁሉአቀፍ/ኩሏለማዌው የሰብአዊ መብቶች መግለጫ፣ (Universal declaration on human rights, ((UDHR)) ፣የሲቪል እና የፖለቲካ መብቶች አለማቀፍ ቃልኪዳን (International covenant on Civil and Political rights (ICCPR)) ፣ የኢኮኖሚ፣ ማህበራዊና የባህላዊ መብቶች አለማቀፍ ቃልኪዳን (International Covenant on Economic, cultural and social rights (ICESCR)) የተባሉ ዓለም-አቀፍ የሰብአዊ መብት ሕግጋት ወጥተው ወደ ስራ ገብተዋል። ለምሳሌ ያህል የሁሉአቀፍ/ኩላዌው የሰብአዊ መብቶች መግለጫ አንቀጽ (2) ፣ የሲቪል እና የፖለቲካ መብቶች አለማቀፍ ቃልኪዳን አንቀጽ 2(1) እንዲሁም የኢኮኖሚ፣ማህበራዊና የባህላዊ መብቶች አለማቀፍ ቃልኪዳን 2(2)ን ስንመለከት እንዲህ በማለት አካተዋል

*ተዋዋይ ሀገሮች በዘር፣ በቀለም፣ በጾታ፣ በቋንቋ፣ በሃይማኖት፣ በፖለቲካ ወይም በሌላ አስተሳሰብ፣ በብሔር ወይም በማህበራዊ ምንጭ፣ በሀብት፣ በውልደት ወይም በሌላ አቋም ምክንያት ምንም ዓይነት ልዩነት ሳያደርጉ የተደነገጉትን መብቶች ለማስከበር ተስማምተዋል፡፡*

ከእነዚህ ሕግጋት አገላለጽ ለመረዳት የሚቻለው፣ መብቶቹ ለሁሉም ሰዎች ያለምንም አድሎ ሁለንተናዊ በሆነ መልኩ ሁሉም ሰዎች መብቶቻቸው ተከብረውላቸው እንዲሁም ሰብአዊ ክብራቸው ተጠብቆላቸው መኖር መቻላቸው ለዓለም ልማትና ለፍትሀዊ የኢኮኖሚና ማህበረሰባዊ እድገት ወሳኝ መሆኑን በሁሉም የዓለም ሀገራት መንግስታት የታመነበት መሆኑን ነው።
የሰው ልጆች ተፈጥሮአዊ ክብር እና ዋጋ እኩልና ሊገሰስ የማይችል መሆኑን መገንዘቡ እንዲህ ያለውን መብት ለሁሉም የሚያጎናጽፍ ስለመሆኑ ከኩሏለማዊ የዓለም-አቀፍ የሰብአዊ መብቶች መግለጫ መቅድም ይዘት እንረዳለን።

ሰብአዊ መብቶች ዓለም-አቀፋዊ (universal) እንዲሁም የማይነጣጠሉ (indivisible) ናቸው። ይሁን እንጂ ይህ መርህ በቀዝቃዛው ጦርነት ወቅት የነበሩ የሀገራት ርዕዮተ-ዓለማዊ ልዩነቶች የፈጠሯቸው ያለመግባባቶች ከሰብአዊ መብቶች አፈጻጸም አኳያ በተለይም በየሲቪልና የፖሊቲካ መብቶችና በኢኮኖሚያዊ፣ የባህልና የማህበራዊ መብቶች ተፈጻሚነት ረገድ ክርክሮች

አስነስቶ ነበር። በዚህም ምክንያት፣ መብቶቹን ለመደንገግ የወጡት ሕግጋት ራሳቸው ከስያሜ አንስቶ እስከ ይዘት ድረስ የሚለያዩ ናቸው። ከእነዚህ ሕግጋት መካከል ዓለም-አቀፉ የኢኮኖሚ፣ የማህበራዊና የባህል መብቶች ዓለም-አቀፍ ቃልኪዳን በመባል የሚታወቀው ስምምነት ውስጥ የተካተቱ የሰው ልጆች መሰረታዊ መብቶች በተለይም ለተሟላ እና ፈጣን ተግባራዊ አፈጻጸም ከሚጠይቁት ኢኮኖሚያዊ ሁናቴዎች ጋር በተያያዘ በተወሰነ መልኩ ለየት ያለ ባህርይ እንዳላቸው ይታመናል።

ከላይ ከዘረዘርናቸው ዓለም-አቀፍ ሕግጋት ይዘት አኳያ፣ የሰብአዊ መብቶችንከስያሜ አንጻር፣ የሲቪል፣ የፖሊቲካ፣ የማህበራዊ፣ የኢኮኖሚ እና የባህል መብቶች በማለት ለመክፈል የሚቻል ሲሆን፣ መብቶቹ ካላቸው ባህሪ በመነሳት ደግሞ በተለያየ ትውልድ ማለትም ቀዳማዊ (first generation) ዳህራዊ (second generation)፣ እንዲሁም ደግሞ ሳልሳዊ (third generation) በማለት ምሁራን ይከፍሏቸዋል።

### 1.1.2. የኢኮኖሚ፣ የማህበራዊና የባህል መብቶችና ልዩ ባህሪያቸው

ከላይ ባለው ንኡስ ክፍል ውስጥ እንደተመለከትነው ሰብአዊ መብቶች እንደተደነገጉበት የዓለም-አቀፍ የሰብአዊ መብቶች ስምምነት ዓይነት እና እንደ መብቶቹ ባህሪ፣ የሲቪል፣ የፖሊቲካ፣ የኢኮኖሚ፣ የማህበራዊ እና የባህል መብቶች (Economic, social, and cultural rights (ESCR)) ተብለው ይከፈላሉ። ለዚህ ንኡስ ክፍል ዓላማ ያክል በተለይ የኢኮኖሚ፣ የማህበራዊ እና የባህል መብቶችን ምንነትና ባህሪያቸውን በጥቂቱ ዘርዘር አድርገን እንመለከታለን።

እ.ኤ.አ. በታህሳስ ወር 1966 ተደንግጎ ከወጣው ዓለም-አቀፍ ቃልኪዳን ሰነድ ይዘት ለመገንዘብ እንደሚቻለው፣ የኢኮኖሚ፣ የማህበራዊና የባህል መብቶች በውስጣቸው፤

- የተሟላ ምግብ የማግኘት መብት፣ (rights to adequate food) ፣
- የተሟላ መኖሪያ ቤት፣ (rights to adequate housing) ፣
- የመማር መብት (rights to education) ፣
- የጤና መብት (rights to health) ፣
- የማህበራዊ ዋስትና መብት (rights to social security) ፣
- በባህላዊ እንቅስቃሴዎች ውስጥ የመሳተፍ መብት (rights to take part in cultural life) ፣
- ንጹህ ውሃ የማግኘት እና የንጽህና መብት (rights to water and sanitation) እና
- የስራ መብት rights to work) የሚሉት ይገኙባቸዋል።

ምንም እንኳ እነዚህ መብቶች በአፈጻጸም ረገድ በቀዝቃዛው ጦርነት ወቅት በመንግስታት መካከል አለመግባባት ፈጥረው የነበረ ቢሆንም ከቅርብ አስርት ዓመታት፣ በተለይም ከ1993 የቬናው የሰብአዊ መብቶች መግለጫ (The 1993 Vienna Declaration on human rights) መውጣት በኋላ፣ ወደቀደመው እና በሰብአዊ መብቶች አይነጣጠሌነት ላይ ወደተመሰረው የመብቶቹ አረዳድ እና የሕግ ስርአት አቀራረጽ ተመልሷል። በተለይም ከ2030ው የዘላቂ ልማት አጀንዳ (the 2030 Agenda for Sustainable Development) አውድና በዓለም ላይ እየተከሰቱ የነበሩትንና ያሉትን ቀውሶች፣ ግጭቶችና ልዩ ልዩ ወረርሽኞችን ለመከላከልና ለመቆጣጠር ሊወሰዱ ከሚገባቸው እርምጃዎች አኳያ፣ የእነዚህ መብቶች አስፈላጊነት ይበልጥ ትኩረት እያገኘ መጥቷል።

የኢኮኖሚ፣ ማህበራዊና የባህል መብቶችን ገቢራዊ ከማድረግ አንጻር መንግስታት ሶስት ዓይነት፣ ማለትም የማክበር፣ የመከላከልና የማሟላት ጠቅላላ ግዴታዎች (general obligation) አሉባቸው። ከዚህም ባሻገር፣ በተለይም ደግሞ የእነዚህን፣ የኢኮኖሚ፣ ማኅበራዊና የባህል መብቶችን ገቢራዊነት በተመለከተ፣ መንግስታት ልዩ ግዴታዎች (specific legal obligations) ተጥለውባቸዋል። እነዚህን ልዩ ግዴታዎችን እንደሚከተለው በአጭሩ እንዘረዝራቸዋለን።

***ሀ) እያደየሚሄድ ግዴታ* (progressive realization) ፦** የኢኮኖሚ፣ ґየማህበራዊና የባህል መብቶችን ገቢራዊነት በተሟላ ሁናቴ እውን ከማድረግ አኳያ መንግስታት እያደገ የሚሄድ እውናዊ የማድረግ ግዴታ (obligation to progressive realization) አለባቸው ሲባል፣ በምንም ዓይነት ኢኮኖሚያዊ ሁናቴ ውስጥ ቢሆንም ባላቸው ሀብትና አቅም መጠን በጊዜ ሂደት ባልተቋረጠ መልኩ ሊያድግ የሚገባው ጥረት ማድረግ የሚገባቸው መሆኑን የሚገልጽ መርህ ሲሆን፣ በተለይም

ደግሞ በአንዳንድ በባህሪያቸው ጊዜ የማይሰጡና አጣዳፊ በሆኑ ግዴታዎች ረገድ ወዲያውኑ ለማሟላት ግዴታ ያለባቸው መሆኑን የሚገልጽ ነው።

**ለ) ለአፋጣኞቹ ቅድሚያ የመስጠት ጠንካራ ግዴታ (core obligation that are of immediate nature: minimum essential levels) ፡-** ምንም እንኳ ሀገራት ከላይ በተገለጸው ምክንያት እያደገ የሚሄድ የመብቶቹን እውን መሆን የማረጋገጥ ግዴታ አለባቸው በማለት ላላ ያለ መርህ ያስቀመጠ ቢሆንም፣ ከእነዚህ መብቶች፣ በተለይም ከተወሰኑ አንገብጋቢ ከሚባሉ መብቶች ጋራ በተያያዘ፣ በየአገራቱ ተጨባጭ ሁናቴ ላይ የሚመሰረት ዝቅተኛውን ገቢራዊ የማድረግ መስፈርት የሚያስቀምጡ መሆኑን መረዳት ያስፈልጋል። ለአብነትም አገራት/መንግስታት ለዜጎቻቸው የሚሰጧቸው የጤና ነክ አገልግሎቶች ለሁሉም ዜጋ ቢያንስ መሰረታዊ የሆኑ የህክምና አገልግሎቶችን ማሟላት እንደሚገባቸው የሚያስገድዱ ናቸው።

**ሐ) የመብቶቹ ገቢራዊነት ማሽቆልቆል ክልከላ (the prohibition of retrogression) ፡-** ከየኢኮኖሚ፣ ማህበራዊና የባህል መብቶች ገቢራዊነት መረጋገጥ ጋራ በተያያዘ መንግስታት በተረጋገጠ መልኩ አንድ ጊዜ በዝቅተኛ መስፈርት መጠን ወደ ተግባር ከገቡ በኋላ አፈጻጸማቸው ማሽቆልቆል የማይገባው መሆኑን በአጽንኦት ተገልጸው እናገኛቸዋለን። ለምሳሌ መንግስታት የሚያወጧቸው ፖሊሲዎችና የሚወስዷቸው እርምጃዎች የሰዎችን የተደራሽ የጤና አገልግሎት መብትና የማህበራዊ ዋስትና ተጠቃሚነታቸውን ዝቅ የሚያደርጉ መሆን የለባቸውም።

**መ) የአድሏዊ አተገባበር ክልከላ ፡-** በዚህ ልዩ ግዴታ መሰረት መንግስታት የሚያወጧቸው ሕግጋት፣ የሚቀርጿቸው ፖሊሲዎችና የሚያከናውኗቸው ተግባራት ሁሉ፣ የያዟቸው ዓላማዎች ወይም ሀሳብ ምንም ይሁን ምን፤ እነዚህን ልዩ ግዴታዎች (specific obligations) ፣ ከመድልኦ አልባነት ጠቅላላ መርህ ጋራ በማጣጣም በተለይም በማህበረሰብ ውስጥ ለጉዳት ተጋላጭ ሊሆኑ የሚችሉ የማህበረሰቡ አካላት ተጠቃሚነት የሚያረጋግጡ ልዩ እርምጃዎችን እንዲወስዱ ግዴታ የሚጥል ነው። እንዲህ ዓይነቱ ልዩ ግዴታ አነስተኛ በሆነ የኢኮኖሚና የሀብት ደረጃ ውስጥም ቢሆን ጸንቶ የሚቀጥል ነው። ሊወሰዱ ከሚገባቸው ልዩ እርምጃዎች መካከልም የግብር አጣጣል ለውጥና ማህበራዊ ንቅናቄዎችን እንደሚያካትቱ ከብዙ ዓለም-አቀፍ ተሞክሮዎች እንረዳለን።

**ሰ) ባላቸው ከፍተኛ አቅም መጠን የሚቻለውን ያክል እርምጃ የመውሰድ ግዴታ፡ (Use of maximum available resources) ፡-** በዚህ ልዩ ግዴታ መሰረት፣ ምንም እንኳ ሀገራት ያላቸው ሀብት አነስተኛ ቢሆን ያለቻቸውን ሀብት ወጪ ቆጣቢ፣ ብቁና ውጤታማ በሆነ መልኩ አስፈላጊ ለሆኑ እና በጣም ለሚያስፈልጋቸው የማህበረሰቡ ክፍሎች የታቀዱ እና እያደገ የሚሄድ የመንግስታት፣ መብቶቹን ገቢራዊ የማድረግ ግዴታን፣ ከግንዛቤ ያስገቡ እርምጃዎችን መውሰድ አለባቸው።

### 1.2 የጤና መብት ጽንሰ-ሀሳብ በዓለም-አቀፍ የሰብአዊ መብቶች ሕግጋት ውስጥ

በቀጥታም ባይሆን፣ የጤና መብት በዓለም-አቀፍ ሕግጋት ውስጥ በመጀመሪያ ጥበቃ ያገኘው እ.ኤ.አ. በ1948 በወጣው የኩሏለማዊው የሰብአዊ መብቶች መግለጫ (universal Declaration on human rights (UDHR)) ውስጥ ሲሆን፣ በዚህ መግለጫ አንቀጽ 25 (1) መሰረት.... ማንም ሰው ለእራሱና ለቤተሰቡ ጤንነትና ደኅንነት በቂ በሚሆን የኑሮ ደረጃ የመኖር መብት አለው፤ ይህም ምግብን፣ ልብስን፣ መጠለያን፣ የሕክምና አገልግሎትን፤ አስፈላጊ የሆኑ የማኅበራዊ አገልግሎቶችን ማግኘትና ለስራ አጥነት፤ ለሕመም፣ ለአካል ጉዳት፣ ለባለቤት ሞት፣ ለእርጅና ወይም ለሌሎች ከአቅም በላይ በሆነ ሁኔታ የሕይወት መሰረትን ለሚያናጉ ችግሮች ዋስትና የማግኘት መብትን ይጨምራል።

ከላይ ከተጠቀሰው ድንጋጌ ለመረዳት እንደሚቻለው፣ የጤና መብት በውስጡ ሰፋ ያለና ተግባራዊነቱም ከሌሎች መብቶች መረጋገጥና እውን መሆን ጋር የተያያዘ እንዲሁም ደግሞ የጤና መብት መረጋገጥ ለሌሎቹ መብቶች እውን መሆን መሰረታዊ መሆኑን የሚያመለክት ነው። ለአብነትም ለጤና መብት መረጋገጥ የተመጣጠነ ምግብ፣ የንጹህ መጠጥ ውሃ፣ ደረጃውን የጠበቀ መኖሪያ-ቤት፣ አልባሳትን እና ሌሎችንም የማኅበራዊ ዋስትና መሰረታዊ አላባውያንን የማግኘት መብትን ያካትታል።

ከላይ እንደተጠቀሰው ዓለም-አቀፉ የኢኮኖሚ፣ ማህበራዊና የባህል መብቶች ቃልኪዳን ከያዛቸው መሰረታዊ የሰዎች ልጆች መብቶች መካከል የጤና መብት የሚለው ይገኝበታል። በዚህ ስምምነት አንቀጽ 12(1) መሰረት.... የዚህ ቃል ኪዳን ተዋዋይ አገሮች ማንኛውም ሰው ሊደረስበት ወደሚችል ከፍተኛ የአካልና የአእምሮ ጤንነት ወደ ተሟላበት የኑሮ ደረጃ (to the enjoyment of the highest attainable standard of physical and mental health) የመድረስ መብት ያለው መሆኑን አውቀው ተቀብለዋል።

በዚሁ አንቀጽ ንኡስ ቁጥር 2 ምንባብ መሰረት ይህንን መብት በተሟላ ሁናቴ ገቢራዊ ከማድረግ አኳያ መንግስታት ሊወስዷቸው የሚገቧቸው ወይም የሚገደዱባቸው ልዩ ሕጋዊ ግዴታዎች (specific legal obligations) ተዘርዝረው ይገኛሉ።የቃል ኪዳኑ ተዋዋይ አገሮች የሚወስዷቸው እርምጃዎች የሚከተሉትን ማካተት አለባቸው፡-

ሀ/ ሞተው የሚወለዱትንና ከተወለዱ በኋላ የሚሞቱትን ሕፃናት ቁጥር መቀነስ እና የሕፃናትን ጤናማ እድገት ማመቻቸት፣

ለ/ የአካባቢና የኢንዱስትሪ ንጽሕና አጠባበቅን ማሻሻል፣

ሐ/ ወረርሽኝን፤ አካባቢያዊና ከስራ ጋር የተዛመዱ በሽታዎችን መከላከል፣ ማከምና መቆጣጠር፣

መ/ ሰዎች ሲታመሙ የሕክምና አገልግሎትና እንክብካቤ የሚያገኙበትን አስፈላጊ ሁኔታ ማመቻቸት፣ የሚሉት ይገኙበታል።

እነዚህን የመንግስታት ልዩ ሕጋዊ ግዴታዎችን በጥልቀት ስንመለከታቸው የጤና መብት በውስጡ የሕክምና አገልግሎቶችን ብቻ የያዘ ሳይሆን ከሌሎች ወሳኝ ማኅበረ-ኢኮኖሚያዊ ሁኔታዎችና ሰብአዊ መብቶች ጋራ ተጣጥሞ ሊተረጎም እንደሚገባ እንገነዘባለን። ለምሳሌም፣ ምግብ የማግኘት መብት (the rights to food), መጠለያ የማግኘት መብት (the right to housing), የስራ መብት (the right to work), የትምህርት መብት (the right to education), የሰው ልጆች ተፈጥሯዊ ክብር (human dignity), በህይወት የመኖር መብት (right to life), የመድልኦ-አልባነት መርህ (non-discrimination), የእኩልነት መርህ (equality), ከሚያሰቃይና ኢሰብአዊ ከሆነ አያያዝ ወይም ቅጣት የመጠበቅ መብት (the prohibition against torture), የግል ነጻነት መብት (privacy), የመረጃ ተደራሽነት (access to information), እና የመደራጀት፣ የመሰብሰብና የመንቀሳቀስ ነጻነት (the freedoms of association, assembly and movement)። የሚሉትና ሌሎችም ሰብአዊ መብቶች የጤና መብት ወሳኝ ክፍሎች ናቸው።

ከዚህም በተጨማሪ የድንጋጌው አርቃቂ ኮሚቴ በዓለም የጤና ድርጅት ሕገ-መንግስት መቅድም ላይ ጤና ማለት የሕማም ወይም የጉዳት መኖር ብቻ ሳይሆን የተሟላ የአካል፣ የአእምሮና የማኅበራዊ ደህንነትም ጭምር ነው በሚል ለጤና ከተሰጠው ትርጓሜ ወጣ በማለት እና "ሊደረስበት ወደሚችል ከፍተኛ የአካልና የአእምሮ ጤንነት ወደ ተሟላበት የኑሮ ደረጃ" (to the enjoyment of the highest attainable standard of physical and mental health) የመድረስ መብት አለው የሚል አገላለጽ በድንጋጌው ውስጥ በማካተት፣ የጤና መብት ሕክምና ከማግኘትም በላይ ሰፊ መብት እንደሆነና ለጤናማ ህይወት መኖርና መሻሻል የግድ አስፈላጊ የሆኑ እና ለተግባራዊነቱ የሚያስፈልጉ ሌሎች ማኅበረ-ኢኮኖሚያዊ ወሳኝ ኩነቶችን ማለትም፤ምግብና የተመጣጠነ አመጋገብ (food and nutrition), የመኖሪያ ቤት (housing)፣ የንጹህ መጠጥ ውሃና የጽዳት ተደራሽነት (access to safe and potable water and adequate sanitation) ፣ ደህንነቱ የተጠበቀና ጤናማ የስራ ሁኔታ (safe and healthy working conditions) ፣ እና ጤናማ አካባቢ (a healthy environment) የሚሉትን እንደሚያካትት ያስገነዝባል።

ከድንጋጌው የመጀመሪያ ንኡስ ቁጥር አገላለጽ ለመረዳት እንደሚቻለው የጤና መብት ለሰው ልጆች ሁሉ የሚያጎናጽፈው መብት ሳይታመሙ መኖር የሚል ብቻ ሳይሆን ከዚያም ላቅ ባለ ሁናቴ ሁሉም የሰው ልጆች አእምሮአዊ፣ አካላዊና ማኅበራዊ ጤናቸው ሁለንተናዊ በሆነ መልኩ ተጠብቆና ለዚህ መብት ምሉእነት የሚያስፈልጉ ሌሎች ሰብአዊ መብቶችና ማኅበረ-ኢኮኖሚያዊ ቅድመ ሁናቴዎች ተሟልተውላቸው እንዲኖሩ ማስቻል የሚለውን ጭምር መሆኑን ነው። ከድንጋጌው ንኡስ ቁጥር 2 ዝርዝር የምንገነዘበው ደግሞ መንግስታት በዝቅተኛ ሁኔታ ከላይ የተገለጸውን መብት ለማሟላት ሊያከናውኗቸው የሚገቧቸውን ግዴታዎች ዝግ ባልሆነ መዘርዝር (illustrative list) አቀራረጽ ስልትን በመከተል የጠቀሰ መሆኑንና መንግስታት ሌሎችንም መብቱ በበለጠ ሊረጋገጥ የሚችልበትን የሕግ፣ የፖሊሲና ስትራቴጂ ስልቶችን ሊከተሉ የሚገባመሆኑን በሚያመላክት መልኩ መደንገጉን ነው። በሌላ አገላለጽ የጤና መብት፣ የሰዎችን ነጻነቶችን (freedoms) እና ከመንግስታት የሚጠበቁ ግዴታዎችን (entitlements) በውስጡ የያዘ ሰፋ ያለ መብት ነው። ለምሳሌም የሰዎች ነጻነትን በተመለከተ ማንኛውም ሰው የስነ-ተዋልዶና የጾታዊ ነጻነቱን ጨምሮ አካሉንና ጤናውን የመቆጣጠርና የመጠበቅ መብት፣ ፈቃዱን ላልገለጸበት የሕክምና ነክ አያያዝና ከሕክምና ጋራ የተገናኙ ሙከራዎች እንዳይደረግበት ከመጠበቅ አንስቶ ከሌላ ማንኛውም ዓይነት ከሚያሰቃዩ አያያዞች ነጻ የመሆን መብት ያለው መሆኑን የሚገልጽ ሲሆን ከመንግስታት ከሚጠበቁ ግዴታዎች ጋራ በተያያዘም፣ ለማንኛውም ሰው በእኩል ያለምንም መድልኦ ሊደረስበት የሚችል ከፍተኛ ጥራት ያለው የጤናማ አኗኗር እድሎችን ሊሰጡ የሚገባቸው የጤና አጠባበቅ ስርአቶችን መዘርጋት የሚሉ ይገኙባቸዋል። ሌላኛው የዚህ

መብት ገጽታ፣ በከባቢያዊ፣ በአገራዊና በዓለም-አቀፍ ደረጃ ማንኛውም ጤና ነክ ውሳኔ ሲሰጥ ማኅበረሰቡን ያሳተፈ ሊሆን እንደሚገባው የሚያመለክት መሆኑ ነው።

የጤናው ዘርፍ አገልግሎቶች ትክክለኛ ተፈጥሮ እንደ የመንግስታቱ የእድገት ደረጃን ጨምሮ በብዙ ሁኔታዎች ላይ በመመስረት የሚለያይ ቢሆንም፣ እንደ ንፁህ የመጠጥ ውሃ እና በቂ የንፅህና መጠበቂያ ተቋማት፣ ሆስፒታሎች፣ ክሊኒኮች እና ሌሎች ጤና ነክ ህንጻዎች፣ የሰለጠኑ እና በአገር ውስጥ ተወዳዳሪ ደመወዝ የሚያገኙ የህክምና እና ተያያዥነት ያላቸው በሙያው ውስጥ ወሳኝ የሆኑ ሰራተኞች እና አስፈላጊ መድሃኒቶችን የመሳሰሉ የጤና ጉዳዮችን ያካትታሉ። በሁሉም መልኩ እና በሁሉም ደረጃዎች ውስጥ ግን፣ ጤና የማግኘት መብት የሚከተሉትን ተያያዥነት ያላቸው እና አስፈላጊ ወሳኝ ጉዳዮችን ይይዛል። እነዚህም፤

**ሀ) ተገኝነት** (**availability**):- በጤናው ዘርፍ የሚሰሩ የህዝብ ጤና እና የጤና አጠባበቅ ተቋማት፣ ቁሳቁሶች እና አገልግሎቶች እንዲሁም ፕሮግራሞች፣ በሁሉም አገራት ውስጥ በበቂ መጠን መገኘት አለባቸው። ከላይ እንደተገለጸው የመገልገያዎቹ፣ የቁሳቁሶቹ እና የአገልግሎቶቹ ትክክለኛ ተፈጥሮ እንደ የመንግስት/አገራት የእድገት ደረጃን ጨምሮ በብዙ ሁኔታዎች ላይ በመመስረት ይለያይ እንጂ እንደ ንፁህ የመጠጥ ውሃ እና በቂ የንፅህና መጠበቂያ ተቋማት፣ ሆስፒታሎች፣ ክሊኒኮች እና ሌሎች ጤና ነክ ህንጻዎች፣ የሰለጠኑ እና በአገር ውስጥ ተወዳዳሪ ደመወዝ የሚያገኙ የህክምና እና ሙያዊ ሰራተኞች እና አስፈላጊ መድሃኒቶችን የመሳሰሉ የጤና ጉዳዮች በበቂ ሁናቴ መገኘት አለባቸው።

**ለ) ተደራሽነትና ምቹነት** (**accessibility**)**:-** የጤና ተቋማት፣ እቃዎች እና አገልግሎቶች ያለ አድልዎ ለሁሉም ሰው ተደራሽ መሆን አለባቸው። ተደራሽነትና ምቹነት፣ ቁስ-አካላዊ/ፊዚካላዊ፣ ኢኮኖሚያዊ፣ የተቀባይነትና የጥራት የሚሉ፣ አራት ተደራራቢ ልኬቶች አሉት።

- *ቁስ-አካላዊ/ፊዚካላዊ ተደራሽነትና ምቹነት (physical accessibility) :-* የጤና ተቋማት፣ ቁሳቁሶች እና አገልግሎቶች ለሁሉም በተለይም በጣም ተጋላጭ ለሆኑ ወይም ለተገለሉ የህብረተሰብ ክፍሎች በሕግም ሆነ በተግባር (by law or fact) ፤ በማንኛውም በተከለከሉ ምክንያቶች አድልኦ ሳይደረግባቸው፤ ለሁሉም ተደራሽና ምቹ መሆን አለባቸው። ተደራሽነትና ምቹነት፣ የሕክምና አገልግሎቶችን እና የጤና ጉዳዮችን የሚወስኑ እንደ ንፁህ እና የመጠጥ ውሃ እና በቂ የንፅህና መጠበቂያ ተቋማት ያሉትን፣ የገጠር አካባቢዎችን ጨምሮ፣ ደህንነቱ የተጠበቀ ቁስ-አካላዊ/ፊዚካላዊ ተደራሽነት (physical accessibility) የሚሉትን ያካትታል። ተደራሽነትና ምቹነት ከዚህም በተጨማሪ፣ ለአካል ጉዳተኞች በቂ የሆነ የሕንፃ መዳረሻ መኖርን ይጨምራል።
- *ኢኮኖሚያዊ ተደራሽነት (ተመጣጣኝነት):-* የጤና ተቋማት፣ እቃዎች እና አገልግሎቶች ለሁሉም ሰው ተመጣጣኝ መሆን አለባቸው። ለጤና አጠባበቅ አገልግሎቶች የሚከፈለው ክፍያ እንዲሁም ከጤና መሠረታዊ ጉዳዮች ጋር የተያያዙ አገልግሎቶች በፍትሃዊነት መርህ ላይ የተመሰረቱ መሆን አለባቸው, እነዚህ አገልግሎቶች በግል ተቋማትም ይሰጡ በመንግስት ተቋማት ደረጃ፣ የሚሰጡት በማህበራዊ ደረጃ የተገለሉ ቡድኖችን ጨምሮ ለሁሉም ሰው ተመጣጣኝ መሆን አለባቸው። ፍትሃዊነት፣ ከበለጸጉ ቤተሰቦች ጋር ሲወዳደር ድሃ ቤተሰቦች በጤና ወጪዎች ጫና እንዳይደርስባቸው ማድረግን ይጠይቃል። የመረጃ ተደራሽነትም በዚሁ ውስጥ አብሮ የሚታይ ሲሆን፤ የመረጃ ተደራሽነት፣ የጤና ጉዳዮችን በተመለከተ መረጃን የመፈለግ፣ የመቀበል እና የማስተላለፍ መብትን ያጠቃልላል። ይሁን እንጂ የመረጃ ተደራሽነት የግል የጤና መረጃን ባከበረ አኳኋን በሚሲጢር የመታከም መብትን ሊጎዳው አይገባም።
- *ተቀባይነት :-* ሁሉም የጤና ተቋማት፣ እቃዎች እና አገልግሎቶች የህክምና ስነምግባርን የሚያከብሩ እና ከባህል አንጻር ተገቢ፣ ማለትም የግለሰቦችን፣ የህዳጣን ብሄረሰቦችን፣ ህዝቦችን እና ማህበረሰቦችን ባህል የሚያከብሩ፣ ለስርዓተ-ፆታ እና የህይወት ኡደት መስፈርቶች ተገቢውን ጥንቃቄ የሚያደርጉ እንዲሁም የሚመለከታቸውን ሰዎች የጤና ሁኔታ ሚሲጢራዊነትን ለማክበር እና ለማሻሻል የተነደፉ መሆን አለባቸው።
- ጥራት:- የጤና ተቋማት፣ የሕክምና ቁሳቁሶች እና አገልግሎቶች ጥራት:- በባህል ተቀባይነት ያለው እንዲሁም በሳይንሳዊ እና በህክምና ተገቢ እና ጥራት ያላቸው መሆን አለባቸው። ይህ የተካኑ የህክምና

ባለሙያዎች፣ በሳይንስ የተረጋገጠ እና ጊዜያቸው ያላለፈባቸው መድሃኒቶች እና የሆስፒታል መሳሪያዎች፣ ንጹህ የመጠጥ ውሃ እና በቂ የንፅህና አጠባበቅ መኖርን ይጠይቃል።

በጠቅላላው፣ የጤና መብት በየኢኮኖሚ፣ ማኅበራዊና የባህል መብቶች ዓለም-አቀፍ ቃልኪዳን ውስጥ ከተደነገጉት የመድልኦ-አልባነት እና የእኩል አያያዝ መርሆዎች ጋራ ተጣጥሞ መተርጎም ይገባዋል።

በዓለም አቀፉ ቃልኪዳን አንቀጽ 2(2) እና አንቀጽ 3 መሠረት በጤና አጠባበቅ ተደራሽነት, የጤና አገልግሎትና የሕክምና ቁሳቁሶች የግዢ ሂደትን ጨምሮ በሁሉም ደረጃ፣ በዘር፣ በቀለም፣ በጾታ፣ በቋንቋ፣ በሃይማኖት፣ ፖለቲካዊ ወይም ሌላ አስተያየት፣ ሀገራዊ ወይም ማህበራዊ አመጣጥ፣ ንብረት፣ ልደት፣ የአካል ወይም የአእምሮ እክል፣ የጤና ሁኔታ (ኤችአይቪ/ኤድስን ጨምሮ) ፣ ጾታዊ ዝንባሌ እና የሲቪል፣ ፖለቲካዊ፣ ማህበራዊ ወይም ሌላ አቋም ላይ በመመስረት በጤና ጉዳዮች ላይ የሚደረግ ማንኛውም መድልኦ የተከለከለ ነው።

እንደ ብዙዎቹ ስትራቴጂዎች፣ ከጤና ጋር የተያያዙ አድሎአዊ ድርጊቶችን ለማስወገድ የተነደፉ መርሃ ግብሮች፣ ህግን በማፅደቅ፣ በማሻሻል ወይም በመሻር ወይም መረጃን በማሰራጨት በአነስተኛ የኢኮኖሚ/የሀብት ሁኔታዎች ውስጥም ቢሆን ሊከናወኑ እንደሚገባቸው አፅንዖት ሰጥቶ መመልከት ይገባል። ይህም በከባድ የሀብት ውስንነት ጊዜ እንኳን ተጋላጭ ለሆኑ የህብረተሰብ ክፍሎች በቂና ምክኒያታዊ የሆነ ትኩረት በመስጠት፣ በአንጻራዊ ሁኔታ ዝቅተኛ ወጭ የሚጠይቁ ፕሮግራሞችን በማፅደቅ ጥበቃ ሊደረግላቸው ይገባል።

ከጤና መብት ጋር በተያያዘ፣ የጤና አጠባበቅና የጤና አገልግሎት ተደራሽነት እና እኩልነት ትኩረት ሊሰጠው ይገባል። አገራት/መንግስታት፣ በቂ አቅም ለሌላቸው የኅብረተሰቡ ክፍል አባላት አስፈላጊው የጤና መድህን እና የጤና አገልግሎት መስጫ ተቋማትን የመስጠት እና በአለም አቀፍ ደረጃ በተከለከሉ የጤና አጠባበቅ እና የጤና አገልግሎቶች አቅርቦት ላይ የሚደርስ ማንኛውንም ዓይነት አድልኦ መከላከል፤ በተለይም ዋናውን የጤና አገልግሎት ከማግኘት መብት ጋራ የተያያዘ ግዴታቸውን መወጣት አለባቸው። የግዴታዎች. ያለመከበርና ተገቢ ያልሆነ የጤና ሃብት ስርጭት ግልጽ ወዳልሆነ መድልዎ ሊያመራ ይችላል። ለምሳሌ፣ ኢንቨስትመንቶች (መዋእለ-ነዋዮች) ሰፋ ያለውን የህብረተሰብ ክፍል ተጠቃሚ ከሚያደርጉ የጤና አገልግሎቶች፣ ምርቶች፣ የመጀመሪያ ደረጃ እና የቅድመ መከላከል የጤና አጠባበቅ ስርአቶች ይልቅ፣ ብዙ ጊዜ ለጥቂቶች፣ እና ልዩ እድል/አቅም ላላቸው የህብረተሰቡ ክፍል ብቻ የሚደርሱ ውድ የሆኑ የፈውስ የጤና አገልግሎቶችን ተመጣጣኝ ባልሆነ መንገድ ማድረስ ላይ ትኩረት እንዲሰጡ ያደርጋቸዋል።

የአካልና የአእምሮ ጤንነት መብትን በተመለከተ፣ የአካል ጉዳተኞችን ጉዳይ በሚመለከተው ጠቅላላ ማብራሪያ ቁጥር .5 (general comment no. 5) አንቀጽ/ፓራግራፍ 34 ስር ከሰፈረው ሀተታ ለመገንዘብ እንደሚቻለው፣ የህዝብ/መንግስት ጤና ሴክተሮች ብቻ ሳይሆኑ የግል የጤና አገልግሎት ሰጪዎች እና ፋሲሊቲዎችም ጭምር ከአካል ጉዳተኞች ጋር በተያያዘ አድሎአዊ አሰራር አለመከተላቸውን ማረጋገጥ እንደሚያስፈልግ ነው።

በአንቀፅ 12(1) ላይ ያለው "ከፍተኛው ሊደረስበት የሚችል የጤና ደረጃ" የሚለው ጽንሰ-ሀሳብ፣ ሁለቱንም፣ ማለትም የግለሰቡን ስነህይወታዊ (biological) እና ማህበረ-ኢኮኖሚያዊ ቅድመ-ሁኔታዎች እና የመንግስትን ሀብቶች ግምት ውስጥ ያስገባል። ይሁን እንጂ በመንግስታት እና በግለሰቦች መካከል ባለው ግንኙነት ውስጥ ብቻ ሊታዩ የማይችሉ በርካታ ገፅታዎች አሉ፤ በተለይም ጥሩ ጤና በመንግስት ብቻ ሊረጋገጥ አይችልም፣ ወይም መንግስታት ለሰው ልጅ ጤና መጓደል ምክንያት የሆኑትን ሁኔታዎች ሁሉ መከላከል አይችሉም። ስለዚህ የጄኔቲክ ምክንያቶች፣ ግለሰባዊ የጤና መታወክ ተጋላጭነት እና ጤናማ ያልሆነ ወይም አደገኛ የአኗኗር ዘይቤዎችን ማስተካከል የግለሰብን ጤና በተመለከተ ትልቅ ሚና ሊጫወቱ ይችላሉ። ስለሆነም የጤና አገልግሎቶችን የማግኘት መብት ከፍተኛውን ሊደረስበት የሚችል የጤና ደረጃ እውን ለማድረግ አስፈላጊ የሆኑ የተለያዩ መገልገያዎችን፣ እቃዎች፣ አገልግሎቶችን እና ሁኔታዎችን በተገቢው እና አካታች በሆነ ሁናቴ የመጠቀም መብትን ማክበርም ጭምር እንደሆነ መረዳት ይገባል።

ከዚህም በተጨማሪ የድንጋጌው አርቃቂ ኮሚቴ ድንጋጌውን ሲያብራራው፣ በአንቀጽ 12(1) ስር የተደነገገው የጤና መብት፣ ወቅታዊና ትክክለኛ የሆነ የጤና ክብካቤ ወይም ሕክምና ማግኘት ብቻ ሳይሆን ለጤናማ ህይወት መረጋገጥ በእጅጉ አስፈላጊ የሆኑ እንደ ደህንነቱ የተረጋገጠ ንጹህ የመጠጥ ውሃ እና ብቁ የሆነ ንጽህና መጠበቂያ ተደራሽነት፣ ጤናማነቱ የተረጋገጠ በቂ እና የተመጣጠነ ምግብ አቅርቦት፣ ምቹ የመኖሪያ ቤት፣ ጤናማ የሆነ የስራና ከባቢያዊ ሁናቴ፣ እንዲሁም

ደግሞ የስነ-ተዋልዶና ጾታዊ ጤናን ጨምሮ ከጤና ጋር የተያያዙ ሁለንተናዊ የትምህርትና የመረጃ ተደራሽነት ያሉ ወሳኝ ማኅበረ-ኢኮኖሚያዊ ቅድመ ሁኔታዎችን የማግኘት መብት መረጋገጥን የሚያካትት ሰፊ መብት ነው በማለት ነው።

## ክፍል 2. የአካል ጉዳተኞች መብት እንደሰብአዊ መብት ጉዳይ

የተለያዩ ዓለም-አቀፍ የሰብአዊ መብት ሕግጋት ወጥተው ተግባራዊ ቢደረጉም፣ ሕግጋቱ ግን በቀጥታ የአካል ጉዳተኞችን መብት የሰብአዊ መብት ጉዳይ (issue of human right) አድርጎ ከመመልከት አንጻር ቀጥተኛ ተፈጻሚነት አልነበራቸውም።ከዚህ አኳያ የአካል ጉዳተኝነት ጉዳይ በተለያዩ የማኅበረሰባዊ ግንዛቤ ደረጃ ዎች ውስጥ በማለፍ አሁን ላለንበት ደረጃ ደርሷል።ቀደም ሲል አካል ጉዳተኝነት በተለያዩ የእሳቤ ማእቀፎች ውስጥ እንዲያልፍ ሆኗል። እነዚህ የአስተሳሰብ ማእቀፎች በተለይም አካል ጉዳተኝነትን ከመገንዘብ አንጻር፣ በአራት ደረጃዎች የሚከፈሉ ሲሆን፤ እነዚህም፤

- የሕክምና ሞዴል፣
- የምጽዋት ሞዴል፣
- የማኅበራዊ ሞዴል እና
- የሰብአዊ መብት ሞዴል ተብለው ይከፈላሉ።

የሕክምና ሞዴል የሚባለው አካል ጉዳተኝነትን እንደ አንድ የጤና እክል አድርጎ የሚወስድና እክሉ ሊስተካከል የሚችልበትን ስልት ሲቀይስም አካል ጉዳተኛውን በሕክምና ካለበት እክል እንዲላቀቅ በማድረግ ብቻ መሆኑን ይገነዘባል። እንዲህ ዓይነቱ ሞዴል ደግሞ አካል ጉዳተኝነት በሕክምና መዳን ካልቻለ አካል ጉዳተኛው በዓለም-አቀፍ የሰብአዊ መብት ሕግጋት ውስጥ እንደማንኛውም ሰው የተጎናጸፋቸውን መሰረታዊ መብቶች ከማሟላት አኳያ ምን ዓይነት የፖሊሲ፣ የሕግና ሌሎችም ዓይነት ተቋማዊ እርምጃዎች መወሰድ እንዳለባቸው ሳይገልጽ ይቀራል። በዚህም ምክንያት በዚህ መንገድ የአካል ጉዳተኞች መብት ተገቢውን ትኩረት ሳያገኝ ቆይቷል።

ሌላኛው የእሳቤ ማእቀፍ ወይም ሞዴል ደግሞ የምጽዋት ሞዴል የሚባለው ሲሆን በዚህ ሞዴል መሰረት አካል ጉዳተኝነት ሊታዘንለት የሚገባ የሰው ልጆች ላይ የሚከሰት እክል መሆኑንና አካል ጉዳተኞችም፣ በሚደረግላቸው የተለያዩ እርዳታዎች ላይ ተመስርተው ከመኖራቸው ውጪ ሌላ ዓይነት በማኅበረ-ኢኮኖሚ እንቅስቃሴዎች ውስጥ የሚኖራቸውን ሁለንተናዊ ተሳትፎና አካል ጉዳተኞች ለሌላው የማኅበረሰብ ክፍል ሊያደርጉ ከሚችሉት አስተዋጽኦ አኳያ ተገቢ ግንዛቤ ያልያዘ ነበረ። ይህ ሞዴል አካል ጉዳተኞችን እንደሰብአዊ ተፈጥሯቸው መጠን በሌሎቹ የሰብአዊ መብቶች እኩል ተጠቃሚ እና የመብቶቻቸውን እውን መሆን በሚገባ የማይገነዘብ በመሆኑ፣ በአካል ጉዳተኞች መብት እድገት ውስጥ ተገቢውን ሚና ለመጫወት አልቻለም።

የማኅበራዊ የእሳቤ ማእቀፍ ወይም ሞዴል በበኩሉ፣ ከላይ ከተጠቀሱት ሞዴሎች ወጣ ባለ እና ሻል ባለ መልኩ አካል ጉዳተኝነት በግለሰቡ አካል፣ የስሜት ህዋስ እና አእምሮ ላይ ካለው እክል  የሚመጣ ሳይሆን፣ በዚህ እክል ምክንያት ከሚከሰቱ የተለያዩ የአመለካከት መጓደሎች ጋራ የተያያዙ የግንዛቤ እጥረቶች የሚወልዱት የምቹነት መጓደል የሚከሰት ውስንነት መሆኑን ይገነዘባል።በዚህም ምክንያት፣ የሰዎች አካል ላይ የሚታዩ እክሎች እና የአስተሳሰብ/የግንዛቤ  ጉድለቶች የሚፈጥሩትን የምቹነት መጓደል በማስተካከል ሁለንተናዊ የአካል ጉዳተኞችን መብት ማረጋገጥ ይቻላል የሚል እሳቤ ያራምዳል።

የአካል ጉዳተኞች መብት እንደ ሰብአዊ መብት ጉዳይ ተብሎ የሚታወቀው የእሳቤ ማእቀፍ ከላይ ከተገለጹት የእሳቤ ማእቀፎች በተለየ ሁኔቴ አካል ጉዳተኞች እንደማንኛውም የማኅበረሰብ ክፍል በሰብአዊ መብቶች ማእቀፍ ውስጥ የተቀመጡ እንደ የሰብአዊ ክብር እና ነጻነት ተጠቃሚ የሆኑና በአካል ጉዳታቸው ምክንያት ሊሟሉ የሚገባቸውን ሌሎችንም መብቶች ጨምሮ ጥበቃ ሊደረግ የሚገባቸውን ሁሉንም ዓይነት መብቶችን ጨምሮ ባልተጓደለ መልኩ ሊጠበቅላቸው የሚገባ መሆኑን የሚገነዘብ እና ከፍተኛ የአስተሳሰብ ለውጥ ያሳየ ማእቀፍ ነው።  ይህ የእሳቤ ማእቀፍ በሌሎች የሰብአዊ መብቶች ድንጋጌዎች ውስጥ ከፍተኛ ተቀባይነት ያላቸውን፣ የእኩልነት (equality)፣ የሰብእና ክብር (dignity) እና የመድልኦ-አልባነት (non-discrimination) መርሆዎችን መሰረት በማድረግ የተነሳ እሳቤ ሲሆን፣ የሰው ልጆች እንደሰው ክብራቸውና መብታቸው ተጠብቆላቸው ለመኖር የግድ አካል ጉዳተኝነታቸውን ማስወገድ ሳያስፈልግ ከነ አካል ጉዳታቸውም ቢሆን ለሌሎቹ ሰዎች የተሟሉ ከሰብእና ጋራ የተገናኙ ሁሉ ነገሮች ሊሟሉላቸው የሚገባ መሆኑን አበክሮ የሚያምን እና እራሱን አካል ጉዳትንም ቢሆን እንደ አንድ የሰብእና መለያ (one part of human diversity) ምልክት አድርጎ መቀበል እንደሚያስፈልግ አጽንኦት ሰጥቶ የሚያምን የእሳቤ ማእቀፍ ነው። በሌላ አገላለጽ፣ አካል ጉዳተኝነት በሕክምና ሊስተካከል የሚገባው፣ የሌሎችን ድጋፍ ብቻ ተንተርሶ ለመኖር የሚያበቃ እክል ነው ወይም ደግሞ በእክሉ እና

በሌሎች ማኅበረሰባዊ አመለካከቶች መጓደል ጥምረት የሚፈጠር ውስንነት ነው ብሎ ከማመን ይልቅ ከነችግሮቹ አስፈላጊ የሆኑ የማመቻቸትና ማሟላት ሁናቴዎችን በማካተት አስገዳጅነት ባለው መልኩ በሕግ ሊደነገግ የሚገባው የመሰረታዊ መብቶች እና ግዴታዎች መንስኤና ውጤት የሆነ ጉዳይ ነው ብሎ መቀበል የሚያስፈልግ መሆኑን ማመን ነው።

## 2.1. የአካል ጉዳተኝነት ብያኔ በዓለም-አቀፉ የአካል ጉዳተኞች መብት ስምምነት ውስጥ

አካል ጉዳተኝነት በተለያየ ጊዜና የዓለም ክፍል/አካባቢ የተለያየ ትርጓሜ የሚሰጠው በሰዎች ላይ የሚፈጠር ክስተት ነው። ከዚህም በተጨማሪ ለአካል ጉዳተኝነት የሚሰጠው ትርጓሜም ቢሆን ግልጽ ያልሆነ፤ አሻሚ እና በቀላሉ ሊያግባባ የማይችል ጽንሰ-ሀሳብ ሆኖ ቆይቷል። ከቅርብ ጊዜ ወዲህ በተለይም ደግሞ ከአካል ጉዳተኞች መብት ኮንቬንሽን መውጣት በኋላ አካል ጉዳተኝነት እያደገ የሚሄድና አጭር፣ ግልጽ እንዲሁም ሁሉንም በተመሳሳይ የሚያግባባ ሳይሆን፣ ቀስ በቀስ እያደገ የሚሄድ ጽንሰ ሃሳብ መሆኑንና የአካል ጉዳት እክሎች ያሉባቸውን ግለሰቦች ከሌሎች አቻዎቻቸው ጋር በእኩል ደረጃ በኅብረተሰቡ ውስጥ ምሉእና ውጤታማ ተሳትፎ ከማድረግ በሚገቷቸው የአመለካከትና አካባቢያዊ መሰናክሎች መካከል ባለው መስተጋብር የሚመጣ ክስተት መሆኑን በመግለጽ፣ ኮንቬንሽኑ በመቅድሙ ፊደል ተራ (ሰ) ስር የማኅበራዊ ሞዴል አረዳድን በሚቀበል አኳኋን ደንግጎ እናገኘዋለን።

ይኸው ኮንቬንሽን ይህንን ጽንሰሀሳብ በተወሰነ ደረጃ ዘርዘር በማድረግ፣ በአንቀጽ 1 ስር፣ አካል ጉዳተኝነት ለሚለው ሐረግ በቀጥታ ትርጉም ከመስጠት ይልቅ "አካል ጉዳተኞች" "የተለያዩ መሰናክሎች ከሚያስከትሏቸው ተጽእኖዎች የተነሳ" ከሌሎች አቻዎቻቸው ጋር በእኩል ደረጃ በማህበረሰቡ ውስጥ ምሉእና ውጤታማ ተሳትፎ እንዳያደርጉ ሊገድቡ ከሚችሉ የረዥም ጊዜ አካላዊ፣ አእምሮአዊ፣ ሥነ-አእምሮአዊ ወይም የስሜት ህዋሳት እክሎች ያሉባቸውን ወገኖች ያጠቃልላሉ" በማለት ዝግ ባልሆነ አብነታዊ አዘራዘር ዘዴ፣ "እክል" የሚባሉት በሰዎች አካል፣ አእምሮ፣ ስነ-አእምሮ ወይም ስሜት ህዋስ ላይ የሚከሰቱ የረዥም ጊዜ ጉዳቶች እና በእነዚህ ጉዳቶች የተነሳም በእነዚህ ሰዎች ረገድ የሚፈጠሩ የተዛቡ አመለካከቶች እና አመለካከቶቹ በሚፈጥሯቸው ከባቢያዊ መሰናክሎች የተነሳ እነዚህ ሰዎች ከሌሎች አቻዎቻቸው ጋር በእኩል ደረጃ ምሉእና ውጤታማ ተሳትፎ እንዳያደርጉ ሊያግዳቸው የሚችል ክስተት እንጂ በራሱ በአካላቸው፣ በአእምሯቸው፣ በስነ-አእምሯቸው ወይም በስሜት ህዋሳቸው ላይ የሚኖረው እክል ብቻውን የሚፈጥረው ክስተት እንዳልሆነ ያስረዳል።

ይህም ማለት፣ ማንም ሰው በአካሉ፣ በአእምሮው፣ በስነአእምሮው ወይም በስሜት ህዋሱ ላይ እክል ቢኖርም እነዚህን እክሎች ከግምት በማስገባት ሌላው የማኅበረሰብ ክፍል በአመለካከቱም ሆነ በከባቢያዊ ሁናቴው ውስጥ ሊኖሩ የሚችሉትን መሰናክሎች በማስወገድ እነዚህን ሰዎች በተሟላና ውጤታማ በሆነ ተሳትፎ የበኩላቸውን ማኅበረ-ኢኮኖሚያዊ አስተዋጽኦ እንዲያደርጉ የሚያስችላቸውን ምቹ ሁናቴ መፍጠር ከተቻለ እነዚህ ሰዎች እንደማንኛውም የማኅበረሰቡ ክፍሎች በትምህርት በስራም ሆነ በሌላ ዓይነት ዘርፍ ብቁና ውጤታማ ለማድረግ የሚቻል መሆኑን የሚያስገነዝብ ነው። ከዚህ የሕጉ አተረጓጎም የምንገነዘበው ነጥብ፣ እክሎቹ ቢኖሩም ሰው በመሆናቸው ብቻ በተፈጥሯቸው የሚያገኟቸው መብቶች እና እክሎቹ የሚፈጥሯቸው ልዩ ፍላጎቶቻቸው ተጣጥመው እንደማንኛውም የሰው ልጆች መብቶች ተወስደው በሕግ ተደንግገው በሚገባ ገቢራዊ ከሆኑ ለሚገኙበት ማኅበረሰብም ሆነ ለራሳቸው ሁለንተናዊ ጠቀሜታ ያለው፤ እና የማኅበረ ኢኮኖሚያዊ እድገቱ/ልማቱ ወሳኝ ክፍል ተደርጎ መወሰድ የሚገባው መሆኑን ነው። ለምሳሌም የአካል ጉዳተኞችን የጤና መብት ብንወስድ እንደማንኛውም የማኅበረሰቡ ክፍል በሕግ የተቀመጠው የጤና መብት ተጠቃሚ መሆን አለባቸው ብሎ ከመውሰድም በተጨማሪ ለእነርሱ ፍላጎት በሚመጥን ደረጃ እና ሁናቴ የጤናውን ዘርፍ አገልግሎት በተለይም የሕክምና መሳሪያዎችን፣ መድኃኒቶችን፣ የሆስፒታል ህንጻዎችን እንዲሁም ደግሞ የሕክምና ሙያተኞችን በስነ-ምግባርም ሆነ በክህሎት በማብቃትና ምቹ እና ተደራሽ በማድረግ አካታች የሆነ፣ ሁሉንም በእኩል ሊያሳትፍ እና ተጠቃሚ ሊያደርግ በሚችል ሁኔታ መቅረጽ ያስፈልጋል።

እንዲህ ባለው የማኅበራዊ እና የሰብአዊ መብቶች የእሳቤ ማእቀፍ ላይ በመመስረት በሌሎች ዓለም-አቀፍ የሰብአዊ መብቶች ቃልኪዳኖችና ስምምነቶች ውስጥ የተደነገጉትን መሰረታዊ መብቶች ከግንዛቤ በማስገባት የራሱ የሆነ ጠቅላላ መርሆዎች እና የልዩ መብቶች ዝርዝር ያሉት፣ በአካል ጉዳተኞች መብቶች አረዳድ ረገድ ፈር ቀዳጅ እና ከፍ ያለ የዕይታ ለውጥ የፈጠረ ዓለም-አቀፍ የአካል ጉዳተኞች መብት ኮንቬንሽን (Convention on the rights of persons with disability) ተብሎ የሚጠራ ዓለም-አቀፍ የሰብአዊ መብቶች ሰነድ እ.ኤ.አ. በ2006 ወጥቶ ተግባራዊ ሆኗል። ይህ ሰነድ፣ የእኛን አገር ኢትዮጵያን ጨምሮ፣ በበርካታ አገራት ተቀባይነት ያገኘ፣ የራሱ የሆነ አፈጻጸሙን የሚከታተል ኮሚቴ ያለው፣ ቀደም ሲል ወጥተው ከነበሩት ስምንት ያክል ዓለም-አቀፍ የሰብአዊ መብት ስምምነቶች ጋራ ተደምሮ ዘጠነኛው የሕግ ሰነድ ሆኖ የተቆጠረ ነው።

### 2.2. የዓለም-አቀፉ የአካልጉዳተኞች መብት ስምምነት ጠቅላላ መርሆዎች እና ጠቅላላ ግዴታዎች

#### 2.2.1. ጠቅላላ መርሆዎች

የዓለም-አቀፉ የአካል ጉዳተኞች ስምምነት አንዱ መገለጫው፣ ለስምምነቱ አተረጓጎም እና ሁለንተናዊ አፈጻጸም የሚያግዙ፣ መሰረታዊ የሆኑ እና በጠቅላላውም በአካል ጉዳት እና አካል ጉዳተኝነት ጽንሰ-ሀሳብ ውስጥም ላቅ ያለ አዎንታዊ አስተዋጽኦ የሚያደርጉ፣ እንዲሁም የስምምነቱ መሰረት የሆኑ፤ በአንቀጽ 3 ስር የተደነገጉት ጠቅላላ መርሆዎቹ ናቸው። እነዚህም፤

- በግል ምርጫ የመወሰን ነፃነትና ራስን ችሎ የመኖር መብትን ጨምሮ ለተፈጥሯዊ ክብርና ለግለሰብአዊ ልዕልና ዋጋ መስጠት፤
- መድልኦ-አልባነት፤
- የተሟላና፣ ውጤታማ ተሳትፎ እና ማኅበረ-ሰብአዊ ተካታችነት፤
- ለልዩነቶች ዋጋ መስጠትና አካል ጉዳተኞችን እንደ ማንኛውም የሰብአዊ ጥንቅርና የሰው ዘር ክፍል አድርጎ መቀበል፤
- የእድሎች እኩልነት፤
- ምቹነትና ተደራሽነት፤
- የወንዶችና የሴቶች እኩልነት፤
- በማደግ ላይ ላለው የአካል ጉዳተኛ ህፃናት ሁለንተናዊ አቅምና በማንነታቸው አጠባበቅ ረገድ ላላቸው መብት አክብሮት ማሳየት የሚሉት ናቸው።

የዓለም-አቀፍ ሰብአዊ መብቶች ሕግጋት ሁሉም ሊባል በሚችል መጠን የሚጀምሩት የሰዎችን ልጆች ሰብአዊ ክብር እና ከሰብእናቸው ጋራ አብሮ የተፈጠረውን እኩልነት ለሰብአዊ መብቶች እና መሰረታዊ ነጻነቶች የማእዘን ድንጋይ ስለመሆናቸው እውቅና በመስጠት ነው። እነዚህ ከላይ የዘረዘርናቸው በዓለም-አቀፉ የአካል ጉዳተኞች ስምምነት ውስጥ የተካተቱት መሰረታዊ መርሆዎች ግን ከነዚህም ሰፋ በማድረግ ለአካል ጉዳተኞች መብት በልዩ ሁናቴ ተፈጻሚ የሚሆኑ በርከት ያሉ ጽንሰ-ሀሳቦችን አካትቷል። ከእነዚህ በልዩ ሁናቴ በስምምነቱ ውስጥ ከተካተቱ ለየት ያሉ ጽንሰሀሳቦች መካከልም፣ የመድልኦ-አልባነት (non-discrimination) ፣ የእድሎች እኩልነት (equality of opportunity) እና ለልዩነት ዋጋ መስጠት (respect for difference) የሚሉት መርሆዎች የሚገኙበት ሲሆን፣ በተለይም ደግሞ የዚህ ስምምነት ጠቅላላ መርሆዎች፣ በግል ነጻነት የመወሰንና ራስን ችሎ መኖር (autonomy)፣ ነጻነት (independence)፣ ተሳትፎና ማኅበረሰብአዊ ተካታችነት (participation, and inclusion in society) የሚሉት የአካል ጉዳተኞችን መብቶች በተሟላ ሁናቴ ከማክበር፣ ማስከበርና ማሟላት ጋራ በተያያዘ በእጅጉ አስፈላጊ ናቸው።

ምንም እንኳ ነጻነት፣ የራስን እድል መወሰን እና መድልኦ-አልባነት የሚሉት ጽንሰ-ሀሳቦች በሌሎችም የሰብ አዊ መብት ሕግጋት ውስጥ ያሉ ቢሆንም፣ በግል ነጻነት የመወሰንና ራስን ችሎ መኖር (autonomy)፣ ነጻነት (independence)፣ ተሳትፎና ማኅበረሰብአዊ ተካታችነት የሚሉት ጽንሰ-ሀሳቦች ግን በሌሎቹ ሕግጋት ውስጥ በቀጥታ የሉም ብቻ ሳይሆን ቃላቱን ከነ ሙሉ ሀሳባቸው ሲጠቀሟቸው አይታይም። የአካል ጉዳተኞች መብት ስምምነት ግን እነዚህን መርሆዎች በቀጥታ በማካተት፣ መርሆዎቹ የአካል ጉዳተኞችን ሰብአዊ መብቶች እውን ለማድረግና ለማረጋገጥ ያላቸውን ሚና አጉልቶ ለማሳየት ችሏል።

#### 2.2.2. ጠቅላላ ግዴታዎች

የዓለም-አቀፉ የአካል ጉዳተኞች ስምምነት በአንቀጽ 4 ስር፣ የአካል ጉዳተኞች መብቶች በተሟላ ሁናቴ እንዲረጋገጡና መንግስታትም በአካል ጉዳት ላይ የተመሰረተ አንዳች ዓይነት መድልኦ ማድረግ ሳያስፈልግ፣ ለአካል ጉዳተኞች በመላ የሁሉንም ሰብአዊ መብቶችና መሠረታዊ ነፃነቶች ምሉእ ተፈፃሚነት ለማረጋገጥ፣ ለማሳደግ እንዲሁም የማክበር፣ የመጠበቅና የማሟላት ግዴታዎቻቸውን በሚገባ እንዲወጡ ለማድረግ የሚያስችሉ ልዩ የአፈጻጸም እርምጃዎችን ወይም ተግባራትን (specific actions) በግልጽ ይዘረዝራል።

እነዚህ ተግባራትም፤

- በስምምነቱ ውስጥ እውቅና ለተሰጣቸው መብቶች ተግባራዊነት ተገቢ ሆነው ያገኟቸውን ሕጋዊ፣ አስተዳደራዊና ሌሎች እርምጃዎችን ሁሉ ለመውሰድ፤
- ሕግ ማውጣትን ጨምሮ በአካል ጉዳተኞች ላይ አድልኦ የሚያስከትሉ በስራ ላይ ያሉ ሕግጋትን፣ ደንቦችን፣ የቆዩ ልማዶችንና አሰራሮችን ለማሻሻል ወይም ለማስወገድ ተገቢ ሆነው የተገኙትን እርምጃዎች ሁሉ ለመውሰድ፤
- በየትኛውም ፖሊሲና መርሃ-ግብር ውስጥ የአካል ጉዳተኞች ሰብአዊ መብት ተካትቶ ጥበቃ እንዲያገኝና ተስፋፍቶ እንዲሰራበት ለማድረግ፤
- ከዚህ ስምምነት ጋር ተፃራሪ ሆኖ በሚታይ በማናቸውም ተግባር ወይም ልማዳዊ አሰራር ተሰማርቶ ከመገኘት ለመቆጠብና የመንግስት ባለስልጣናትም ሆኑ ተቋማት ስራቸውን ከስምምነቱ ጋር በተጣጣመ ሁኔታ ስለማከናወናቸው ለማረጋገጥ፤
- አካል ጉዳተኝነትን ተንተርሶ በማንኛውም ግለሰብ፣ ተቋም ወይም የግል ድርጅት አማካኝነት የሚፈፀምን መድልኦ ለማስወገድ፤
- የአካል ጉዳተኞችን የተለያዩ ፍላጎቶች ግምት ውስጥ በማስገባት የተቻለውን ያህል ክንውኑ የሚጠይቀው የማስማማት ስራ ዝቅተኛና የሚያስከትለው ወጪም አነስተኛ ሆኖ እስከተገኘ ድረስ፣ በስምምነቱ አንቀጽ 2 ሥር እንደተተረጎመው ሁሉን አቀፍ ንድፍን ተከትለው የሚደራጁ እቃዎችን፣ አገልግሎቶችን፣ መሣሪያዎችንና ማቀላጠፊያዎችን አሻሽሎ በማውጣት ላይ ያተኮሩ የምርምርና የልማት ሥራዎችን ለማከናወን ወይም እንዲከናወኑ ለማድረግ የሚበጁትን እርምጃዎች ሁሉ ለመውሰድ፤ የነዚህኑ ምርቶችና የአገልግሎቶች አቅርቦትና አጠቃቀም ለማሳደግና በደረጃዎችም ሆነ በመመሪያዎች ዝግጅትና አወጣጥ ረገድ እንዲሁ ሁሉን አቀፍ ተቀባይነት የሚኖረው ንድፍ ተቀርጾ በስራ ላይ እንዲውል ለማድረግ፤
- በተመጣጣኝ ዋጋ ለሚገኙት ቅድሚያ በመስጠቱ ላይ አተኩረው የመረጃና የመገናኛ ቴክኖሎጅዎችን፣ የእንቅስቃሴ መርጃ መሳሪያዎችንና ድጋፍ ሰጭ መገልገያዎችን ጨምሮ ለአካል ጉዳተኞች ተስማሚነት ባላቸው አዳዲስ ቴክኖሎጅዎች ዙሪያ የምርምርና የልማት ስራዎችን ለማካሄድ፣ ይኸው እንዲካሄድ ለማነሳሳትና አቅርቦታቸውንም ሆነ አጠቃቀማቸውን ከፍ ለማድረግ፤
- አዳዲስ ቴክኖሎጅዎችን፣ እንዲሁም ሌሎች የመርጃ መንገዶችን፣ የድጋፍ አገልግሎቶችንና ማቀላጠፊያዎችን ጨምሮ የእንቅስቃሴ መርጃ መሳሪያዎችንና ደጋፊ ቴክኖሎጅዎችን አስመልክቶ ለአካል ጉዳተኞች ተደራሽነት ባለው ዘዴ መረጃዎችን ለመስጠትና
- በእነዚያው መብቶች አማካኝነት የተረጋገጡትን ድጋፎችና አገልግሎቶች በላቀ ውጤታማነት ለመስጠት ይቻላቸው ዘንድ በዚህ ስምምነት እውቅና ባገኙት መብቶች ዙሪያ ከአካል ጉዳተኞች ጋር አብሮ ለሚሰሩ ሙያተኞችና ደጋፊ ሠራተኞች የሚሰጠውን ስልጠና ከፍ ለማድረግ የሚሉት ይገኙባቸዋል።

በዚህ ድንጋጌ ስር የሰፈሩ አብዛኛዎቹ የመንግስታት ጠቅላላ ግዴታዎች በሌሎችም የሰብአዊ መብቶች ሕግጋት ውስጥ የተዘረዘሩ ሲሆኑ፣ የተወሰኑቱ በተለይም፣ ሁሉን አቀፍ ንድፍን ተከትለው የሚደራጁ እቃዎችን፣ አገልግሎቶችን፣ መሣሪያዎችንና ማቀላጠፊያዎችን እንዲሁም ደግሞ ተደራሽ እና አሳላጭ የሆኑ ቴክኖሎጂዎችና እቃዎች ላይ የሚደረጉ ምርምሮችን የሚመለከቱት ግዴታዎች ለአካል ጉዳተኞች ስምምነት ብቻ የተሰጡ ልዩ መገለጫዎች ናቸው። እነዚህ ልዩ የሆኑ በተለይም ደግሞ ለአካል ጉዳተኞች መብቶች መረጋገጥ ይበልጥ አስፈላጊ ይሆናሉ ተብለው የተካተቱ የመንግስታት ልዩ ግዴታዎች፣ በስምምነቱ ውስጥ ያሉትን ሌሎች መብቶችንም ጭምር ሁለንተናዊ በሆነ መልኩ ለማረጋገጥ አስፈላጊና መሰረታዊ መሆናቸውን መረዳት ያስፈልጋል።

የዚህ ሁሉን አቀፍ ድንጋጌ ዋነኛው ዓላማ፣ በታሪክ ውስጥ የነበሩትንና መንግስታት የአካል ጉዳተኞችን መሰረታዊ ሰብአዊ መብቶች እንደ ወሳኝ የሰው ልጆች መብቶች አድርጎ ያለመመልከት የፈጠረውን ግድፈት ለመድፈን ነው። እንደሚታወቀው መንግስታት ከዚህ ቀደም እንዲህ ዓይነቶቹን ተግባራት የሚያከናውኗቸው ለአካል ጉዳተኞች ካለ ልዩ የሆነ አያያዝ ወይም ደግሞ በማኅበራዊ ግዴታን መወጣት መልኩ እንጂ የግድ የሚሉ የሰብአዊ መብቶች መስፈርቶችን የማሟላት አድርገው አልነበረም። በመሆኑም እነዚህ ግዴታዎች በዝርዝር መቀመጣቸው እንዲህ ያለውን ጎጂ አስተሳሰብ ለመከላት ትልቅ እርምጃ ወደ ፊት እንደመራመድ የሚቆጠር ነው።

እነዚህ ከላይ የተገለጹ አናቅጽን ጨምሮ ሌሎች ወሳኝ የሚባሉ በራሳቸው አስፈላጊ ከመሆናቸውም በላይ በስምምነቱ ውስጥ ለተጠቀሱ ሌሎች መብቶች ተግባራዊ አፈጻጸም አስፈላጊነት ያላቸው ድንጋጌዎች አሉ። ከእነዚህ መካከልም፤ በአንቀጽ 5 ስር የተጠቀሰው የእኩልነት እና የመድልኦ-አልባነት መርህ፣ በአንቀጽ 8 ስር የተጠቀሰው የግንዛቤ ማስፋፋት መርህ እና የተደራሽነት መርህ የሚሉት ዋነኞቹ ናቸው። የእነዚህን መሰረታዊ መርሆዎች አስፈላጊነት በጽሁፉ ዋና ክፍል ውስጥ ስንገባና በዝርዝር ስንመለከት በበለጠ እንረዳዋለን። የአካል ጉዳተኞች መብቶች ስምምነት በጠቅላላ መርህ ደረጃ ከዘረዘራቸው መርሆዎች በተጨማሪ ልዩ የሚባሉ መብቶችንም በዝርዝር በውስጡ ይዟል። እነዚህ መብቶች በተለየ ሁናቴ የአካል ጉዳተኞችን ጉዳይ በቀጥታከመያዛቸው በቀር በሌሎች ሕግጋት ውስጥ የተካተቱ ናቸው። ይሁን እንጂ፣ በተለይም በአንቀጽ 19 ስር የተደነገገው በነጻነት ለብቻ የመኖር እና በማኅበረሰብ ውስጥ የመካተት መብት (Living independently and being included in the community) ፣ በአንቀጽ 20 ስር የተጠቀሰው በግል እራስን ችሎ የመንቀሳቀስ መብት (Personal mobility) እንዲሁም በአንቀጽ 26 ስር የተገለጸው የማቋቋምና ተሀድሶ መብት (Habilitation and Rehabilitation) የሚሉት ለአካል ጉዳተኞች በተለየ ተፈጻሚነት ያላቸው ናቸው።

## ክፍል 3. የጤና መብት በዓለም-አቀፉ የአካል ጉዳተኞች ስምምነት ውስጥ

የሰው ልጆች የጤና ጉዳይ የየሰዉን የእለት ተእለት አኗኗርና የጠቅላላውን ማኅበረሰብ ኢኮኖሚያዊ፣ ፖሊቲካዊ እና ማኅበረሰባዊ ግንኙነትም ሆነ ሁናቴ ለመወሰን የሚችል አንገብጋቢ ጉዳይ ነው። በዚህም ምክንያት ዋና ዋና በሚባሉ፣ እንደ የኩሉዓለማዊ የሰብአዊ መብቶች መግለጫና የኢኮኖሚያዊ፣ ማኅበረሰባዊ እና የባህል መብቶች ዓለም-አቀፍ ቃልኪዳን ባሉ የሰብአዊ መብት ስምምነቶችም ሆነ በአለም ጤና ድርጅት ማቋቋሚያ እና መተዳደሪያ ሰነድ ማለትም በዓለም የጤና ድርጅት ሕገ-መንግስት ውስጥ ትኩረት ካገኙ መሰረታዊ የሰው ልጆች መብቶች መካከል አንዱ እና ዋነኛው ነው። ከፍተኛ ደረጃ ያለው የጤና አጠባበቅ መብት የሚለው፣ መሰረታዊው የጤና መብት ጽንሰ-ሀሳብ በመጀመሪያ ጥበቃ ያገኘው፣ እ.ኤ.አ. በ1946 በወጣው የዓለም የጤና ድርጅት ሕገ-መንግስት ውስጥ ሲሆን ይህ ሰነድ በመቅድሙ ላይ ጤና ማለት የህመም ወይም የጉዳት መኖር ያለመኖር ብቻ ሳይሆን የሰው ልጆች የተሟላ አካላዊ፣ አእምሮአዊ እና ስነልቡናዊ ደህንነትን የሚመለከት ጉዳይ ነው ሲል የሚገልጽ ሲሆን፤ ይኸው ሕገ-መንግስት ከዚህ በተጨማሪም የሰው ልጆች በዘራቸው፣ በሃይማኖታቸው፣ በኢኮኖሚያዊ ሁኔታቸው፣ በፖሊቲካም ሆነ በማኅበራዊ አመለካከታቸው ላይ በመመስረት ምንም ዓይነት ልዩነት ሳይደረግባቸው የከፍተኛ ደረጃ የጤና አገልግሎት ተጠቃሚ መሆን የሚለው ጽንሰ-ሀሳብ የመሰረታዊ የሰብአዊ መብቶች ጥበቃ አካል መሆኑን ይገልጻል።

ከዚሁ ነጥብ ጋራ በተያያዘም፣ የኩሉዓለማዊው የሰብአዊ መብቶች መግለጫ በአንቀጽ 25 ስር ጤና የተሟላ እና ደረጃውን የጠበቀ አኗኗር (adequate standard of living) አንዱ መገለጫ መሆኑን የሚደነግግ ሲሆን፤ ከዚህ ድንጋጌ አገላለጽ ለመገንዘብ የሚቻለው፣ ጤና ያለመታመም ብቻ ሳይሆን የሰው ልጆች ሁለንተናዊ ማለትም አካላዊ፣ ስነልቡናዊ እና አእምሮአዊ ደህንነቱ እንዲጠበቅለት ሊሟሉ የሚያስፈልጉ የአኗኗር ዘዬዎችን ጨምሮ የመሰረታዊ ፍላጎቶችን በተለይም ንጹህ ውሃ የተሟላ መኖሪያ ቤት እና የመሳሰሉትን የሚያካትት መሆኑን ነው። ከዚህ ድንጋጌ ጋራ በሚጣጣም መልኩ፣ እ.ኤ.አ. በ1966 የወጣው የዓለም አቀፉ የኢኮኖሚ፣ ማኅበራዊ እና የባህል መብቶች ቃልኪዳን አንቀጽ 12(1) የጤና መብት የሰብአዊ መብቶች ክፍል መሆኑን በድጋሜ በማረጋገጥ ይገልጻል። ከነዚህ ጠቅላላ ዓለም-አቀፍ የሰብአዊ መብቶች ስምምነት በተጨማሪም የዓለም አቀፉ የአካል ጉዳተኞች ስምምነት፣ ተዋዋይ መንግስታት አካል ጉዳተኞች በጉዳተኝነታቸው ላይ የተመሰረተ መድልኦ ሳይደረግባቸው በከፍተኛ ደረጃ በሚገኘው የጤና አጠባበቅ መብት የመጠቀም መብት እንዳላቸው ይገነዘባሉ፤ ተዋዋይ መንግስታት ከጤና ጋር ተያያዥነት ያለውን ተሃድሶ ጨምሮ አካል ጉዳተኞች ፆታ-ተኮር በሆኑ የጤና አገልግሎቶች የመጠቀም ዕድል ያላቸው ስለመሆኑ ለማረጋገጥ የሚያስፈልጉትን ተገቢ እርምጃዎች ሁሉ የሚወስዱ ሲሆን እነርሱም ቀጥሎ የተመለከቱት ይሆናሉ፤

ሀ) የፆታና የሥነ ተዋልዶ ጤና አጠባበቅና አህዝቦትን መሰረት ያደረጉ የሕዝብ ጤና ፕሮግራሞችን ጨምሮ ለሌሎች ሰዎች በሚሰጠው ደረጃ አንድ ዓይነት ርቀት፣ ጥራትና ደረጃ ያላቸው ነፃና በቀላሉ ሊገኙ የሚችሉ የጤና አጠባበቅ ፕሮግራሞችን ለአካል ጉዳተኞች ማቅረብ፤

ለ) እንደተገቢነቱ ከመነሻው በጊዜ መለየትንና ጣልቃ መግባትን ጨምሮ ይልቁንም በጉዳተኝነታቸው ምክንያት የሚያስፈልጋቸውን የጤና አገልግሎት ለአካል ጉዳተኞች ማቅረብና እንዲሁም ሕፃናትና አረጋዊያንን በተመለከተ ተጨማሪ አካል ጉዳተኝነትን ለመቀነስና ለመከላከል የታቀዱ አገልግሎቶችን መስጠት፤

ሐ) ገጠራማ አካባቢዎችን ጨምሮ እነዚህን የጤና አገልግሎቶች በተቻለ ቅርበት ለራሱ ግለሰቡ በሚገኝበት ማኅበረሰብ ማቅረብ፤

መ) ነፃ የሆነና በዕውቀት ላይ የተመሰረተ ፈቃድን ጨምሮ ለመንግስትና ለግል የጤና እንክብካቤ መስጫ ተቋማት በሚሰጥ ስልጠናና በሚደነገግ የሙያ ሥነ ምግባር ደረጃ አማካኝነት ስለአካል ጉዳተኞች ሰብአዊ መብቶች ከበሬታ፣ የግል ነፃነትና ልዩ ፍላጎቶች ያላቸውን ግንዛቤ በማሻሻል የጤና ባለሙያዎች ለአካል ጉዳተኞች ከሌሎች ጋር አንድ አይነት የሆነና ጥራቱን የጠበቀ የጤና አገልግሎት እንዲሰጡ ማድረግ፤

ሠ) በብሔራዊ ሕግ ውስጥ በተገቢና ምክንያታዊነት ባለው አግባብ ተፈቅዶ ሲገኝ በጤናና በሕይወት መድህን አገልግሎቶች አሰጣጥ ረገድ የአካል ጉዳተኞችን መድልኦ መከልከልና

ረ) በአካል ጉዳተኝነት ላይ ተመስርቶ በጤና እንክብካቤ፣ በጤና አገልግሎቶች፣ በምግብና በፈሳሾች አቅርቦት የሚደረገውን አድሏዊ የመንፈግ ድርጊት መከላከል ያለባቸው መሆኑን በመግለጽ በዝርዝር ይደነግጋል።

ከላይ ከተገለጸው ድንጋጌ አንጻር ከዚህ ዓለም አቀፍ ስምምነት ለመገንዘብ የሚቻለው፣ አካል ጉዳተኞች በአካል ጉዳታቸው ላይ የተመሰረተ ምንም ዓይነት መድልኦ ሳይደረግባቸው "በከፍተኛ ደረጃ በሚገኘው የጤና አጠባበቅ መብት" የመጠቀም መብት እንዳላቸው፤ ቀጥተኛ በሆነ መልክ እራሱን አካል ጉዳተኝነትን ከግንዛቤ በማስገባት የጤና መብት ከመድልኦ ነጻ በሆነ መልኩ እንደማንኛውም ሰብአዊ መብት ጥበቃ ሊደረግለት የሚገባ መሆኑን የሚያስገነዝብ ነው። ከዚህ ጉዳይ ጋራ የሚገናኘው ነጥብ "በከፍተኛ ደረጃ በሚገኘው የጤና አጠባበቅ መብት" የሚለው ሐረግ እንዴት መተርጎም አለበት የሚለው ነው። ይህንን ሐረግ በሚገባ ለመገንዘብም የአንቀጽ 25 ድንጋጌ ይዘት በአካል ጉዳተኞች መብቶች ስምምነት አንቀጽ 3 ስር ከተደነገጉት መድልኦ-አልባነት (non-discrimination) ፣ በግል ምርጫ የመወሰን ነፃነትና ራስን ችሎ የመኖር መብት (autonomy)፣ የተሟላና፣ ውጤታማ ተሳትፎና ማኅበረ-ሰብአዊ ተካታችነት (participation)፣ ጾታዊ እኩልነት (gender equality) እና የእድሎች እኩልነት (equality of opportunity) ከሚሉት መሰረታዊ መርሆዎች እና እንዲሁም ደግሞ በአንቀጽ 4(2) ስር ከተደነገገው እያደገ የሚሄድ የአገራት ግዴታ ከሚለው ጠቅላላ ግዴታ ጋራ በማሰናሰል መረዳት ያስፈልጋል።

ከአካል ጉዳተኞች መብት ስምምነት አንቀጽ 25 ይዘት ለመረዳት የሚቻለው ለአካል ጉዳተኞች የጤና መብት ጥበቃ ማድረግ የሚለው ጽንሰ-ሀሳብ እራሱ አካል ጉዳት እንደ የሕክምና ጉዳይ መሆኑን ብቻ ሳይሆን ለሌሎቹ ለአካል ጉዳት አልባ ሰዎች የተሰጠው የመሰረታዊ መብት ጥበቃ ለአካል ጉዳተኞችም ጭምር በእኩል ደረጃ እና ጥራት ያለመድልኦ ሁለንተናዊ በሆነ መልኩ ሊረጋገጥ የሚገባ የአካል ጉዳተኞች የሰብአዊ መብት አካል መሆኑንም ጭምር ነው። ይህ ማለት ደግሞ የጤና መብት በዓለም-አቀፉ የኢኮኖሚ፣ ማኅበራዊና የባህል መብቶች ቃል ኪዳን ስር ጥበቃ የሚደረግለት ሰብአዊ መብት መሆኑንና እንዲህ ያሉት መብቶች ካላቸው ባህሪ አንጻር ደግሞ በመንግስታት ላይ እያደገ የሚሄድ የማስተግበር ግዴታ የሚጥሉ መሆናቸው የሚታወቅ ስለሆነ ይህንን ፍሬ-ነገር ከአካል ጉዳተኞች ስምምነት በተለይም ደግሞ ከጤና መብት አንጻር ያለውን አንድምታ መመልከት በእጅጉ አስፈላጊ ይሆናል።

## 3.1. እያደገ የሚሄድ ገቢራዊ የማድረግ ግዴታና የመድልኦ አልባነት መርህ

እንደ የጤና መብት ያሉ በኢኮኖሚ፣ በማኅበራዊና በባህል መብት ውስጥ የሚካተቱ መብቶችን ገቢራዊ ከማድረግ አኳያ መንግስታት እያደገ የሚሄድ ገቢራዊ የማድረግ ግዴታ አለባቸው ሲባል፣ ባልተቋረጠ እና በተቻለ መጠን እና ፍጥነት እነዚህን መብቶች በተሟላ ሁናቴ ገቢራዊ ለማድረግ የሚያስችላቸውን ሁሉንም ዓይነት እንቅስቃሴ የማድረግ ልዩ ግዴታ አለባቸው ማለት ነው። በዚህም መሰረት የአካል ጉዳተኞች መብቶች ስምምነት በአንቀጽ 4(2) ስር.... ኢኮኖሚያዊ፣ ማህበራዊና ባሕላዊ መብቶችን በሚመለከት በዓለም-አቀፍ ሕግ መሠረት ወዲያውኑ ተፈፃሚ እንዲሆኑ ታስበው በዚህ ስምምነት ውስጥ የተካተቱት ግዴታዎች እንደተጠበቁ ሆነው፣ እያንዳንዱ ተዋዋይ መንግስት ደረጃ በደረጃ የተጠቀሱትን መብቶች እውን መሆን ሙሉ በሙሉ ለማሳካት አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝ በዓለም-አቀፋዊ የትብብር ማዕቀፍ ተጠቃሚ መሆኑ ሳይቀር ራሱ ባለው ሀብት አንፃር ከፍተኛ ሆኖ የተገኘውን እርምጃ ሁሉ እንዲወስድ ይገደዳል.... በማለት፣ በዚሁ ሕግ አንቀጽ 25 ስር የተደነገገው ልዩ የሆነው የጤና መብት ከዚህ በጠቅላላ ግዴታነት ከተደነገገው የአገራት ግዴታ አንጻር ሊታይ የሚገባው መሆኑን ያመለክታል። ይህ ማለት ደግሞ የአካል ጉዳተኞች መብቶች ኮሚቴ (The Committee on the Rights of Persons with Disabilities) ሕጉን በማርቀቅ ወቅትም ቢሆን አገራት በሕጉ በተፈለገው መጠን ወዲያውኑ መብቱን ተግባራዊ ሊያደርጉት እንደማይችሉና ይህንን መብት ባልተቋረጠና እያደገ በሚሄድ መጠን የመብቱን ገቢራዊነት የሚያረጋግጡ ተግባራትን የማከናወን ግዴታ ያለባቸው መሆኑን ከግንዛቤ ያስገባ መሆኑን የሚያመለክት ነው። ይህንን መብት ወዲያውኑ ገቢራዊ ለማድረግ ለምሳሌ ያክል የጤና ክብካቤ መአከላት መሰረተ-ልማትን ማብልጸግ፣ የጤና ባለሙያዎችን ማሰልጠን ወይም የጤናውን ዘርፍ ሕግጋት ማሻሻል ወ:ዘ:ተ ተግባራትን የማከናወን ግዴታዎች ሊኖርባቸው የሚችል በመሆኑ፣ ይህንን ከግንዛቤ በማስገባት አገራት ለዚህ ግዴታቸው እውን መሆን ሲሉ አስፈላጊውን ሁሉ ባልተቋረጠና እያደገ በሚሄድ ልክ ተግባራዊ ግዴታቸውን መወጣት ያለባቸው መሆኑን በመቀበል ግዴታ የገቡ መሆኑን መረዳት ይቻላል።

ይሁን እንጂ አገራት ይህንን በሚያደርጉበት ጊዜ ተግባራቸውን ያለምንም መድልኦ የሁሉንም ሰዎች መብቶች ባማከለ አኳኋን ልዩ የሆነ ፍላጎት ያላቸውን የማኅበረሰቡ አካላት መብትና ጥቅምም ጭምር በእኩል ደረጃ ከግንዛቤ አስገብተው መስራት ይገባቸዋል። ይህንን ደግሞ አገራት በተለይም ደግሞ የአካል ጉዳተኞችን መብቶችን የሚደነግገውን ዓለም-አቀፍ

ስምምነት ተቀብለው ባጸደቁበት ወቅት ወዲያውኑ ገቢራዊ ለማድረግ ከተስማሙባቸው ግዴታዎቻቸው መካከል፣ በዚሁ ሕግ ውስጥ ያሉ ሌሎችን መብቶች ገቢራዊነት ምሉእ እንዲያደርጋቸው ታስቦ የተዘጋጀውን፣ የመድልኦ አልባነት መርሆ የሚለውን በማየት መገንዘብ ይቻላል። በአካል ጉዳተኞች መብቶች ዓለም-አቀፍ ስምምነት ውስጥ የተደነገገው የመድልኦ-አልባነት መርህ በተለይም አካል ጉዳትን መሰረት ያደረጉ ልዩነቶች ወይም አድሏዊ አሰራሮችን ለማስወገድ ቁርጠኛ የሆነ መሆኑን ከአንቀጽ 3፣ 4 እና ከሌሎቹም ልዩ መብቶችን ከሚደነግጉት አናቅጽ ይዘት ለመረዳት ይቻላል። በመሆኑም፣ የኢኮኖሚ፣ ማኅበራዊ እና የባህል መብቶችን ገቢራዊ በማድረግ ሂደትም ውስጥ አገራት የሚወስዷቸው ባልተቋረጠ ሁናቴ እያደጉ የሚሄዱ እርምጃዎች ይህንን ግዴታቸውን ከግንዛቤ ያስገባ፣ ከዚሁ ጋራ የተጣጣመና የግድ መፈጸም ያለበት እና አካል ጉዳተኞች ከሌላው የማኅበረሰብ ክፍል ጋራ እኩል በሆነ መልክ በእነዚህ መብቶቻቸው ተጠቃሚ እንዲሆኑ የማድረግ ግዴታ አለባቸው ማለት ነው።

መድልኦ-አልባነትን የማረጋገጥ ግዴታ በውስን የሀብት/ኢኮኖሚ ሁኔታ ውስጥም ወዲያውኑ ሊረጋገጥ የሚገባው መሆኑን ከየኢኮኖሚ፣ ማኅበራዊና የባህል መብቶች ኮሚቴ (The Committee on Economic, Social and Cultural Rights) ማብራሪያ ለመገንዘብ ይቻላል። በዚህ የኮሚቴው ማብራሪያ መሰረት" .... non-discrimination is an immediate obligation for all States, regardless of resources because "many measures, such as most strategies and programmes designed to eliminate health-related discrimination, can be pursued with minimum resource implications through the adoption, modification or abrogation of legislation or the dissemination of information...." የመድልኦ-አልባነት መርሆ በሁሉም አገራት ላይ ያላቸውን የኢኮኖሚ ሁናቴ ከግምት ሳያስገባ፣ ወዲያውኑ ሊተገበር የሚገባው ግዴታ መሆኑን እና በተለይም ከጤናው ጋራ የተገናኙ ይህንን ግዴታ ለማረጋገጥ የሚወሰዱ እርምጃዎች በአነስተኛ ወጪ ሊረጋገጡ የሚችሉ መሆናቸውን፣ ይልቁንም እንደ አዲስ ሕግ ማውጣት፣ ማሻሻል ወይም ያሉትን ሕግጋት ወደ አንድ አምጥቶ በማጠቃለል ወይም መረጃዎችን በማሰራጨት ሊረጋገጥ የሚችል በመሆኑ ነው።

ይህ የአገራት ግዴታ የአካል ጉዳተኞች መብቶች ስምምነትን ሲያጸድቁ በበለጠ ከአካል ጉዳተኝነት ጋራ የተገናኙ አድሏዊ አሰራሮችን ለማስወገድ ግዴታ የገቡ መሆኑን የሚያመለክት ነው። በዚሁ ሕግ አንቀጽ 2 መሰረት፣ በአካል ጉዳት ላይ የተመሠረተ መድልኦ" ማለት በፖለቲካዊ፣ ኤኮኖሚያዊ፣ ማኅበራዊ፣ ባህላዊ፣ በሲቪል ነክ ወይም በሌላ በማናቸውም መስክ ሰብዓዊ መብቶችንና መሠረታዊ ነፃነቶችን ሁሉ ከሌሎች ጋር በእኩልነት ደረጃ ከመጠቀም ወይም ተግባራዊ ከማድረግ ወይም ለነዚሁ መብቶችና ነፃነቶች እውቅና ከመስጠት የመገደብ ዓላማ ወይም ይህንኑ ዓይነት ውጤት የሚያስከትል ማናቸውም ልዩነት፣ አግልሎት ወይም ተፅዕኖ ነው። አድራጎቱ ምክንያታዊ ተቀባይነት ያለው ማስተካከያ አለማቅረብን ወይም ይህንኑ መንፈግን ጨምሮ ሁሉንም ዓይነት የመድልኦ ተግባራት ያካትታል። ከዚህ የጠቅላላ ግዴታ አገላለጽ እና በአካል ጉዳት ላይ የተመሰረተ መድልኦ ለሚለው ሐረግ ከተሰጠው ትርጓሜ ይዘት ለመረዳት የሚቻለው ነጥብ፣ አገራት ይህንን ግዴታቸውን በሚወጡበት ጊዜ የአካል ጉዳተኞችን ጉዳይ ወደ ጎን በማድረግ ወይም በተገቢው ከግንዛቤ ሳያስገቡ በመቅረት የሚወስዷቸው የሕግ፣ የፖሊሲ፣ የተቋም እና ሌሎችም ዓይነት የለውጥ እርምጃዎች እንደ መድልኦ የሚቆጠር መሆኑን ነው።

በዚህም መሰረት የጤና መብትን እውን ለማድረግ በጤናው ዘርፍ የሚወሰዱ ማንኛውም ዓይነት እርምጃዎች ዘርፉ ለሌሎች ሰዎች ሊሰጥ በሚችለው ጥራት መጠን አካል ጉዳተኞችም በእኩል ደረጃ ተጠቃሚ እንዲሆኑ የሚያስችል እና በተደራሽነት እና ምቹነት መርሆ ያለምንም መድልኦ ሊከናወን የሚገባው መሆኑን መገንዘብ ያስፈልጋል።

### 3.2. የተደራሽነትና ምቹነት መርሆና የጤና አገልግሎት

አካል ጉዳተኞች የጤናውን ዘርፍ አገልግሎቶች ከመጠቀም አኳያ፣ ከአገልግሎቱ ዋጋ መናር፣ ተደራሽነትና ምቹነት፣ መገለልና መድልኦ አንስቶ ከናካቴው ያለመኖር ወይም ያሉትም ደግሞ በበቂ ጥራት ያለመገኘት ድረስ ያሉ ዘርፈ ብዙ መሰናክሎች የሚደርሱባቸው መሆኑ ይታወቃል። አካል ጉዳተኞች እኩል የጤና አገልግሎት ማግኘት ካልቻሉ፣ ለዘገየ የጤና ምርመራ (delayed diagnoses) ፣ ለሁለተኛ ደረጃ በሽታዎች (secondary co-morbidities) ፣ ለዘለቄታዊ መጎሳቆል (persistent abuse) ፣ ለተሟጠጠ ማህበራዊ ካፒታል (depleted social capital) እና መገለል (isolation) ለመሳሰሉ የከፋ አደጋ ሊጋለጡ ይችላሉ። ይህንን ከግንዛቤ በማስገባትም የአካል ጉዳተኞች መብቶች ጥበቃ ስምምነት፣ አገራት የጤናውን ዘርፍ ተደራሽነት ለማረጋገጥ እና ለአካል ጉዳተኞች ምቹ ለማድረግ የሚያስችሉ እርምጃዎችን እንዲወስዱ ያስገድዳል።

የአካል ጉዳተኞች መብቶች ጥበቃ ስምምነትም ሆነ የኢኮኖሚ፣ የማኅበራዊ እና የባህል መብቶች ኮሚቴ (Committee on Economic, Social and Cultural Rights) (CESCR) ተደራሽነት ምን ማለት እንደሆነ እና ከጤናው አኳያ እንዴት መረዳት እንደሚያስፈልግ የሚያመለክቱ መራሄ ሀሳቦችን (guidance) ይዘረዝራሉ። ከዚህ አንጻር የአካል ጉዳተኞች መብቶች ጥበቃ ስምምነት በአንቀጽ 9 ስር.... አካል ጉዳተኞች ኑሯቸውን በነፃነት እንዲመሩና በየትኛውም የሕይወት መስክ ያልተገደበ ተሳትፎ እንዲያደርጉ ለማስቻል፣ ተዋዋይ መንግሥታት እነዚሁ ወገኖች ከሌሎች አቻዎቻቸው ባልተናነሰ ሁኔታ ቁስ-አካላዊ ከባቢን የመድረስም ሆነ በመጓጓዣ ዘዴዎች፣ የመረጃና የመገናኛ ቴክኖሎጂዎችንና ስርዓቶችን ጨምሮ በመረጃና መገናኛ አውታሮች እንዲሁም በከተማም ይሁን በገጠር ለሕዝብ ክፍት በተደረጉ ተቋማትና አገልግሎቶች የመጠቀም ዕድል የተመቻቸላቸው መሆኑን ለማረጋገጥ ተገቢነት ያላቸውን እርምጃዎች ይወስዳሉ.... በማለት የሚደነግግ ሲሆን፤ በተደራሽነት ላይ የተጋረጡትን መሰናክሎችና ገደቦች መለየትና ማስወገድን የሚያጠቃልሉት እነዚህ እርምጃዎች ከሁሉ በፊት ቀጥሎ በተመለከቱት ላይ ተፈፃሚዎች ይሆናሉ በማለት ቅድሚያ የሚሰጣቸውን ታሳቢዎች በግልጽ ይዘረዝራል። በቅድሚያ እንዲታዩ በማለት ከዘረዘራቸው መካከልም፤

ሀ) ሕንፃዎች፣ መንገዶች፣ የመጓጓዣ ዘዴዎችና እንደ ትምህርት ቤቶች፣ የመኖሪያ ሥፍራዎች፣ "የሕክምና አገልግሎት መስጫ ድርጅቶችና" የስራ ማከናወኛ ቦታዎች ያሉ የቤት ውስጥና የቤት ውጭ መገልገያ ተቋማት ይበልጥ አንገብጋቢ መሆናቸውን ከግምት በማስገባት ለነዚሁ ቅድሚያ ተሰጥቶ እንዲሰራ በማለት በመጀመሪያው ረድፍ ላይ ገልጿል።

ለ) የኤሌክትሮኒክና የአስቸኳይ ጊዜ አገልግሎቶችን ጨምሮ የመረጃ፣ የመገናኛና ሌሎች አገልግሎቶች የሚሉትን ደግሞ በቀጣዩ መዘርዝር ውስጥ አካትቷል።

ይኸው አንቀጽ በንኡስ ቁጥር 2 ስር መንግስታት በተጨማሪ ከዚህ በታች የተመለከቱትን በስራ ላይ ለማዋል ተገቢ እርምጃዎችን ይወስዳሉ በማለት በዝርዝር ሊወሰዱ የሚገባቸውን ተግባራት ይገልጻል። በዚህ ድንጋጌ ስር መንግስታት እንዲያከናውኗቸው የተጠቀሱ ተግባራት፤

> ሀ) ለሕዝብ ክፍት የተደረጉ ወይም የተመቻቹ ተቋማትንና አገልግሎቶችን ለመድረስ የሚያስችሉ ዝቅተኛ መስፈርቶችንና መመሪያዎችን ማዘጋጀት፣ በይፋ ማውጣትና ተግባራዊነታቸውን መቆጣጠር፤
>
> ለ) ለሕዝብ ክፍት የሆኑ አገልግሎቶችን በማመቻቸትና በማቅረብ ስራ ላይ የተሰማሩ የግል ድርጅቶች እነዚሁ አገልግሎቶች ለአካል ጉዳተኞች ጭምር ተደራሽነት እንዲኖራቸው አስፈላጊ የሆኑትን ጉዳዮች ሁሉ ግምት ውስጥ ማስገባታቸውን ማረጋገጥ፤

ሐ) አካል ጉዳተኞችን በሚገጥሟቸው የተደራሽነት ችግሮች ዙሪያ ጉዳዩ ለሚመለከታቸው ወገኖች ስልጠና መስጠት፤

መ) ለሕዝብ ክፍት በሆኑ ሕንፃዎችና ሌሎች መገልገያ ተቋማት ውስጥ በግልጽ የሚታዩ ምልክቶችን፣ ብሬሎችንና በቀላሉ አንብቦ ለመረዳት የሚያስችሉ ቅጾችን ማስቀመጥ ወይም ማቅረብ እና ሠ) የቀጥታ ድጋፍ ዓይነቶችንና መሪዎችን፣ አንባቢያንንም ሆነ በምልክት ቋንቋ አጠቃቀም የሰለጠኑ አስተርጓሚዎችን ጨምሮ ለሕዝብ ክፍት የሆኑ ሕንፃዎችንና ሌሎች መገልገያ ተቋማትን ተደራሽነት የሚያመቻቹ አማካዮችን ዝግጁ ማድረግ የሚሉት ይገኙባቸዋል።

የኢኮኖሚ፣ ማኅበራዊና የባህል መብቶች ኮሚቴ የጤናን ጉዳይ በሚመለከተው በጠቅላላ ማብራሪያ ቁጥር 14 (General Comment 14 on the right to health) ውስጥ ተደራሽነትና ምቹነት በውስጡ አራት መሰረታዊ ይዘቶች እንዳሉት ይገልጻል። እነርሱም፤

- መድልኦ-አልባነት (non-discrimination) ፤
- የቁስ-አካላዊ ተደራሽነት (physical accessibility) ፤
- ኢኮኖሚያዊ ተደራሽነት (economic accessibility) ፤ እና
- የመረጃ ተደራሽነት (information accessibility) የሚሉት ናቸው።

### 3.2.1. መድልኦ-አልባነት እና የእኩል ተጠቃሚነት

የመድልኦ-አልባነት መርሆ በአካል ጉዳተኞች መብቶች ጥበቃ ስምምነት ውስጥ ዋና እና መአከላዊ ነጥብ መሆኑ ግልጽ ነው። ይህ መርሆ አካል ጉዳተኞች በጤናው ዘርፍ ሊኖራቸው ከሚፈለገው የእኩል ተጠቃሚነት መብት መረጋገጥ ጋራ በተያያዘ መሰረታዊ የሆነ የሕጉ ፍሬ-ነገር ነው።

ከላይ እንደተገለጸው በስምምነቱ ውስጥ መድልኦ" ማለት በፖለቲካዊ፣ ኤኮኖሚያዊ፣ ማኅበራዊ፣ ባህላዊ፣ በሲቪል ነክ ወይም በሌላ በማናቸውም መስክ ሰብዓዊ መብቶችንና መሠረታዊ ነፃነቶችን ሁሉ ከሌሎች ጋር በእኩልነት ደረጃ ከመጠቀም ወይም ተግባራዊ ከማድረግ ወይም ለነዚሁ መብቶችና ነፃነቶች እውቅና ከመስጠት የመገደብ ዓላማ ወይም ይህንኑ ዓይነት ውጤት የሚያስከትል ማናቸውም ልዩነት፣ አግልሎት ወይም ተፅዕኖ ነው ከማለትም አልፎ አድራጎቱ ምክንያታዊ ተቀባይነት ያለው ማስተካከያ አለማቅረብን ወይም ይህንኑ መንፈግን ጨምሮ ሁሉንም ዓይነት የመድልኦ ተግባራት ያካትታል በሚል ሰፋ ተደርጎ ተተርጉሟል። በመሆኑም አካል ጉዳተኞች እንደማንኛውም የማኅበረሰቡ ክፍል በጤናው ዘርፍ በእኩልነት እንዲገለገሉ የሚያስችሉ ሁለንተናዊ ለውጦችን ያለማድረግ በዚሁ የሕጉ ትርጓሜ መሰረት መድልኦ መሆኑን መረዳት ያስፈልጋል። በተለይም ደግሞ ከቅርብ ጊዜ ወዲህ እየመጣ ካለው አካል ጉዳተኞችን በአንድ መአከል ውስጥ ከማቆየት ይልቅ ወደ ማኅበረሰባዊ አኗኗር የመለወጥ እቅድ አንጻር የጤና ነክ አገልግሎቶች እና ተቋማት ልማት ለአካል ጉዳተኞች አመቺ በሆነ፣ አካታች እንዲሁም ተደራሽ እና ምቹ በሆነ መልኩ ሊካሄድ የሚገባው መሆኑን የሚያስረዳ ነው።

### 3.2.2. ቁስ-አካላዊ ተደራሽነት (Physical Accessibility)

ቁስ-አካላዊ ተደራሽነት የሚለው የጤናውን ዘርፍ ተደራሽነት ለአካል ጉዳተኞች ምቹ ከማድረግ አኳያ በእጅጉ አስፈላጊ ነው። አካል ጉዳተኞች በጤናው ዘርፍ ከሚያጋጥማቸው ቁስ-አካላዊ መሰናክል ውስጥ የአካባቢ፣ የመሰረተ-ልማት እና በገጠራማ አካባቢዎች እንደሚያጋጥመው ያለ መልከአ-ምድራዊ መሰናክሎች የሚሉት ይካተቱበታል። የኢኮኖሚ፣ የማኅበራዊና የባህል መብቶች ኮሚቴ ከላይ በተገለጸው ጠቅላላ ማብራሪያ ውስጥ የቁስ-አካላዊ ተደራሽነትን እንደሚከተለው ያብራራዋል። የጤና ነክ ፋሲሊቲዎች፣ እቃዎችና አገልግሎቶች አካል ጉዳተኞችን ጨምሮ ለሁሉም የማኅበረሰብ ክፍሎች በቀላሉ እና አስተማማኝ በሆነ መልኩ ሊደረስበት በሚችል ርቀት ውስጥ መገኘት ይገባቸዋል። እንዲህ ያለው ተደራሽነት የሕክምና አገልግሎትን ብቻ የሚመለከት ሳይሆን ለጤናማ አኗኗር ወሳኝ የሆኑ እንደ የንጹህ መጠጥ ውሃና የንጽህና መጠበቂያ ተቋማት ያሉትንም የሚጨምር ነው። ከዚህም ባሻገር ቁስ-አካላዊ ተደራሽነት አካል ጉዳተኞች በህንጻዎች ላይ ያላቸውን ተደራሽነት የሚያካትት ነው።

ከአካል ጉዳተኞች መብቶች ጥበቃ ስምምነት አንቀጽ 25(ሐ) ይዘት ለመረዳት የሚቻለው መልከአ-ምድራዊ ሁናቴዎች ከግምት የገቡ መሆኑን ሲሆን፣ ገጠራማ አካባቢዎችን ጨምሮ እነዚህን የጤና አገልግሎቶች በተቻለ ቅርበት ለራሱ ግለሰቡ በሚገኝበት ማኅበረሰብ ማቅረብ የሚለው የቁስ አካላዊ ተደራሽነት ዋነኛው ክፍል መሆኑን ነው። የቁስ-አካላዊ ተደራሽነት ከጤና ፋሲሊቲዎችም በተጨማሪ የሕክምና መስጫ ቁሳቁሶችንና አገልግሎቶችንም ጭምር ያካትታል። ለዚህ እንደማሳያም የመንቀሳቀሻ አካል ጉዳት ያለባቸው ሴቶች የጡትና ማህጸን ጫፍ/በር ካንሰር ምርመራ ለማድረግ ይቸገራሉ። ምክንያቱም የምርመራ ጠረጴዛዎቹ ከፍ እና ዝቅ በማለት እንደሁኔታው ሊለዋወጥ የሚችል ባለመሆኑና የማሞግራፊ መሳሪያዎች (mammography equipment) የሚባሉት መሳሪያዎች መቆም የሚችሉ ሰዎችን ብቻ ታሳቢ በማድረግ የተዘጋጁ በመሆናቸው ነው።

### 3.2.3. ኢኮኖሚያዊ ተደራሽነት (economic accessibility)

በአካል ጉዳተኞች መብቶች ጥበቃ ስምምነት አንቀጽ 25(ሀ) መሰረት የፆታና የሥነ ተዋልዶ ጤና አጠባበቅና አህዝቦትን መሰረት ያደረጉ የሕዝብ ጤና ፕሮግራሞችን ጨምሮ ለሌሎች ሰዎች በሚሰጠው ደረጃ አንድ ዓይነት ርቀት፣ ጥራትና ደረጃ ያላቸው ነፃና በቀላሉ ሊገኙ የሚችሉ የጤና አጠባበቅ መርሀ-ግብሮችን ለአካል ጉዳተኞች ማቅረብ። የሚለው ግዴታ፣ በመንግስታት ላይ የተጣለና የአካል ጉዳተኞችን ኢኮኖሚያዊ ሁናቴ ከግምት ያስገባ እና ኢኮኖሚያዊ ተደራሽነትን ለማረጋገጥ የተደነገገ ነው። ይኸውም አካል ጉዳተኞች ከላይ ሲገለጽ እንደነበረው ባለባቸው ማኅበረ-ኢኮኖሚያዊ መገለል ምክንያት በስራም ሆነ በሌላ ኢኮኖሚያዊ እንቅስቃሴዎች ውስጥ ያላቸው ተሳትፎ አነስተኛ በመሆኑና የገንዘብ አቅማቸውም በአብዛኛው ዝቅተኛ በሆነ ደረጃ ላይ የሚገኝ በመሆኑ ከፍተኛ ዋጋ የሚጠይቁ የሕክምና አገልግሎቶችን ከፍለው ሊጠቀሙ አይችሉም። በመሆኑም መንግስታት የጤና አገልግሎቶቻቸውን የአካል ጉዳተኞችን ተጠቃሚነት የሚያረጋግጡ ተግባራትን እንዲያከናውኑ ግዴታ ጥሎባቸዋል። ከዚህም በተጨማሪ፣ ይኸው አንቀጽ በፊደል ተራ (ሠ) ስር በብሔራዊ ሕግ ውስጥ በተገቢና ምክንያታዊነት ባለው አግባብ ተፈቅዶ ሲገኝ በጤናና በሕይወት መድህን አገልግሎቶች አሰጣጥ ረገድ የአካል

ጉዳተኞችን መድልኦ መከልከልና ተገቢውን ጥበቃ ማድረግ የሚገባ መሆኑን ይገልጻል፡፡ እንደሚታወቀው አካል ጉዳተኞች ዝቅተኛ የሆነ የስራ እድል ያላቸው በመሆኑና አብዛሀኛውን ጊዜም የጤና መድህን ሽፋን ደግሞ በቀጣሪዎች ለተቀጣሪዎች የሚገባ በመሆኑ ይህንን እድል ሊያገኙ የማይችሉ አካል ጉዳተኞች መጠን ከፍ ያለ ሆኖ ይታያል፡፡ ይህንን ለማካካስ በማሰብ አካል ጉዳተኞች በራሳቸው የመድህን ሽፋን ለማግኘት ቢያስቡ፣ ባለባቸው የጤና ሁናቴ ላይ በመመስረት የጤናና የህይወት መድህን አረቦን መጨመር እንዳይኖር መከላከል ያስፈልጋል፡፡ በመሆኑም እንዲህ ዓይነቱን የአካል ጉዳተኞችን ኢኮኖሚያዊ ተደራሽነት እድል የሚያጣብቡ ተግባራትን ማስወገድ ያስፈልጋል፡፡

### 3.2.4. የመረጃ ተደራሽነት (information accessibility)

ጤና ነክ መረጃዎች የሚቀርቡባቸው ዓይነቶችም ሆኑ የመረጃዎቹ ይዘት የአካል ጉዳተኞችን የመረጃ ማግኘት መብት ሊያጣብቡ የሚችሉ ሆነው ሊገኙ ይችላሉ፡፡ ስለዚህም በጤናው ዘርፍ የሚሰራጩ መረጃዎች የአካል ጉዳተኞችን የመረጃ ተደራሽነት መብትን ከግምት ያስገቡ ሊሆኑ ይገባል፡፡ ለምሳሌም ያክል የሚወጡ ጤና ነክ መረጃዎችን ለዓይነስውራን በብሬል መስማት ለተሳናቸው ሰዎች ደግሞ በምልክት ቋንቋ ማቅረብ እንዲህ ዓይነት አካል ጉዳት ያለባቸው ሰዎች ሊገጥማቸው የሚችለውን የመረጃ ማግኘት ውስንነት ለማስተካከል የሚወሰዱ ተስማሚ የሆነ የመረጃ አቀራረብ ፎርም ወይም ዓይነቶች ናቸው፡፡ በሌላ በኩል ደግሞ ለመረዳት ቀላል የሆኑ ቋንቋዎችንና ስዕላዊ ወይም የካርቱን ስዕሎችን መጠቀም በአንድ የጤና ነክ መረጃ ማሰራጫ ሰነድ ላይ ሊኖር የሚችለውን የይዘት ውስንነት ለማስተካከል የሚወሰዱ እርምጃዎች ናቸው፡፡

በጤናው ዘርፍ ውስጥ፣ በታካሚውና በሕክምና አገልግሎት ሰጪው መካከል በሚኖረው ግንኙነት ውስጥ የመረጃ ተደራሽነት የሚጫወተው ሚና በእጅጉ አስፈላጊ ነው፡፡ በዚህም መሰረት አካል ጉዳተኛ ታካሚውን በሚገባ አዳምጦ ያለበትን የጤና እክል ተገንዝቦ ሊሰጠው የሚገባውን እርዳታ ለመወሰንና እርሱም ለታካሚው የሚሰጠውን ክብካቤ ዓይነትና ምክንያት ከነውጤቱ ለማስረዳት በመካከላቸው ሊኖር የሚገባው የመረጃ ልውውጥ የግድ አስፈላጊ ነው፡፡ ከዚህም ባሻገር የታካሚውን የጤና መረጃ ሚስጢራዊነት ለማክበርም ቢሆን ይህ መሰሉን የመረጃ ተደራሽነት መስፈርት መደንገጉ አስፈላጊ ይሆናል፡፡ በጤና አገልግሎት አሰጣጥ ዘርፍ አውድ ውስጥ የመረጃ ተደራሽነት በጤና ስርአት ውስጥ በቀጠሮ አሰጣጥ፣ በወረፋ ማስጠበቂያ ሰነዶች፣ በሪፈራል ሰነዶች እንዲሁም ደግሞ በሕንጻዎች ውስጥ ሊኖሩ በሚገባቸው ምልክቶችም ጭምር ሊኖሩ የሚገባቸውን የተደራሽነት መስፈርቶችን ያካትታል፡፡

## 3.3. በመረጃ ላይ የተመሰረተ ነጻ ፈቃድ

የአካል ጉዳተኞች መብቶች ጥበቃ ስምምነት በአንቀጽ 25 ፊደል ተራ(መ) ስር ነፃ የሆነና በዕውቀት ላይ የተመሰረተ ፈቃድን ጨምሮ ለመንግስትና ለግል የጤና እንክብካቤ መስጫ ተቋማት በሚሰጥ ስልጠናና በሚደነገግ የሙያ ሥነ ምግባር ደረጃ አማካኝነት ስለአካል ጉዳተኞች ሰብአዊ መብቶች፣ ክበሬታ፣ የግል ነፃነትና ልዩ ፍላጎቶች ያላቸውን ግንዛቤ በማሻሻል የጤና ባለሙያዎች ለአካል ጉዳተኞች ከሌሎች ጋር አንድ አይነት የሆነና ጥራቱን የጠበቀ የጤና አገልግሎት እንዲሰጡ ማድረግ እንደሚያስፈልግ ይደነግጋል፡፡ እንዲህ ያለው ጥበቃ በአካሚው የጤና ባለሙያ እና በታካሚው አካል ጉዳተኛ መካከል በሚፈጠረው የመረጃ መለዋወጥ ክፍተት ላይ ብቻ የተመሰረተ ሳይሆን በተለይም በአንዳንድ የአካል ጉዳት ዓይነት ማለትም የሳይኮ-ሶሻል እክል ያለባቸውን ሰዎች ለማከም የሕክምና ዘርፉ እስከ ቅርብ ጊዜ ድረስ የሚከተለውን ስልት ከጥያቄ ውስጥ የሚያስገባና ትኩረት እንዲደረግበት የሚያመለክት ነው፡፡

እንደሚታወቀው አእምሮአዊ እና ስነ-አእምሮአዊ እክል ያለባቸው አካል ጉዳተኞችን ለማከም የሚወሰዱ እርምጃዎች በራሳቸው በታካሚዎቹ ፈቃድ ላይ ያልተመሰረተ እና በሞግዚቶቻቸው ወይም በሌላ በማንኛውም ሰው በኩል በሚሰጥ ፈቃድ ላይ የተመሰረተ ነው፡፡ ይሁን እንጂ እንዲህ ያለው የሕክምና ስልት ከአካል ጉዳተኞች በተለይም ከአእምሮ እና ስነ-አእምሮ ጋራ በተያያዙ ጉዳቶች ውስጥ ላሉ ሰዎች የሚሰጠውን ሕክምና የተሟላ እንዳይሆን አድርጎታል፡፡ በዚህም ምክንያት የሕክምና ዘርፉ የተለያዩ ዓይነት በታካሚው በመረጃ ላይ የተመሰረተ ውሳኔ አሰጣጥ እንዲኖር የሚያስችሉ የሕክምና ስነ-ምግባር መለኪያ ደንቦችን በመቅረጽ ላይ ይገኛል፡፡ በመረጃ ላይ የተመሰረተ ስምምነት፣ የሕክምና ጣልቃ ገብነትን (medical intervention) ፣ መቀበል ብቻ ሳይሆን፣ በፈቃደኝነት እና በበቂ መረጃ ላይ የተመሰረተ ውሳኔ, የታካሚውን በሕክምና

ውሳኔ አሰጣጥ ላይ የመሳተፍ መብትን መጠበቅ እና ተዛማጅ ተግባራትን እና ግዴታዎችን ለጤና እንክብካቤ አቅራቢዎች መስጠት (assigning associated duties and obligations to health-care providers) ነው።

ተዛማጅ ተግባራትን እና ግዴታዎችን ለጤና እንክብካቤ አቅራቢዎች መስጠት (assigning associated duties and obligations to health-care providers) የሚለው የስነምግባር ደንብ እና የህግ መደበኛ ማረጋገጫዎች (ethical and legal normative justifications) መነሻ ምክንያቶች፣ የታካሚ በራስ የመወሰን፣ ራስን የመቻል፣ የአካል ነጻነት እና ደህንነት የሚሉ መሰረታዊ ነጥቦች ናቸው። በመረጃ ላይ የተመሰረተ ፈቃድ የሚለው የአካል ጉዳተኞች ጤና መብት ጽንሰ-ሀሳብ በዐለም-አቀፉ የአካል ጉዳተኞች መብቶች ጥበቃ ስምምነት አንቀጽ 3 ፊደል ተራ (ሀ) ስር የተደነገገውን እና በግል ምርጫ የመወሰን ነፃነትና ራስን ችሎ የመኖር መብትን ጨምሮ ለተፈጥሯዊ ክብርና ለግለሰብአዊ ልዕልና ዋጋ መስጠት የሚለውን መሰረታዊ ጠቅላላ መርሆ ከግምት የሚያስገባ ነው። በዚህ መሰረት አካል ጉዳተኞች ስለሚደረግላቸው ሕክምና በሚገባ አውቀውና ተገንዝበው እንዲወስኑ፣ ፈቃዳቸውንም በራሳቸው እንዲሰጡ በመካከል ሊገቡ የሚችሉ ሰዎችን ወይም ሞግዚቶችን ጨምሮ ሌሎችንም በማስቀረት እራሱ የሕክምና ባለሙያው በቀጥታ ከአካል ጉዳተኛ ታካሚዎቹ ጋራ በመገናኘትና በማስረዳት ሕክምናውን ወይም እንክብካቤውን እንዲሰጥ ማስቻል የሚለው ነጥብ አካል ጉዳተኞች ስለሚሰጣቸው ሕክምና ወይም እንክብካቤ ተገንዝበው ፈቃዳቸውን የመስጠት ወይም የመንፈግ መብት እንዳላቸው የሚያመለክት ነው።

### 3.4. የፆታና የሥነ ተዋልዶ ጤና አጠባበቅ

የአካል ጉዳተኞች መብቶች ጥበቃ ስምምነት በአንቀጽ 25 ፊደል ተራ (ሀ) ስር የፆታና የሥነ ተዋልዶ ጤና አጠባበቅና አሀዝቦትን መሰረት ያደረጉ የሕዝብ ጤና መርሀ-ግብሮችን ጨምሮ ለሌሎች ሰዎች በሚሰጠው ደረጃ አንድ ዓይነት ርቀት፣ ጥራትና ደረጃ ያላቸው ነፃና በቀላሉ ሊገኙ የሚችሉ የጤና አጠባበቅ መርሀ-ግብሮችን ለአካል ጉዳተኞች ማቅረብ አለባቸው ሲል በመንግስታት ላይ ግዴታ ይጥላል።

### 3.5. የጤና ባለሙያዎችን ግንዛቤ እና እውቀት ስለማዳበር

የአንቀጽ 25 ሌላኛው እና መሰረታዊ የሚባለው ይዘቱ ለግልም ሆነ ለመንግስት የሕክምና ተቋማት እና የሕክምና ባለሙያዎች ስለሚሰጥ ስልጠና እና ሊዘጋጁ ስለሚገባቸው የስነምግባር ደንቦች የሚደነግገው ክፍል ነው። በዚህ መሰረት ነፃ የሆነና በዕውቀት ላይ የተመሰረተ ፈቃድን ጨምሮ ለመንግስትና ለግል የጤና እንክብካቤ መስጫ ተቋማት በሚሰጥ ስልጠናና በሚደነገግ የሙያ ሥነ ምግባር ደረጃ አማካኝነት ስለአካል ጉዳተኞች ሰብአዊ መብቶች ከበሬታ፣ የግል ነፃነትና ልዩ ፍላጎቶች ያላቸውን ግንዛቤ በማሻሻል የጤና ባለሙያዎች ለአካል ጉዳተኞች ከሌሎች ጋር አንድ አይነት የሆነና ጥራቱን የጠበቀ የጤና አገልግሎት እንዲሰጡ ማድረግ በሚል በግልጽ ተደንግጎ እናገኘዋለን። ከዚህ የአገራት ግዴታ ለመገንዘብ የሚቻለው ፍሬ-ነገር፣ የሕክምና ባለሙያዎች ከሕክምና ትምህርታቸው ከወጡ በኋላ ስለ አካል ጉዳተኞች ሰብአዊ መብቶች ግንዛቤ መፍጠር ብቻ ሳይሆን በሙያ ተግባራቸውም ውስጥ የሚተዳደሩባቸውን የስነ-ምግባር ደንቦች ከማማውጣትና ተግባራዊ ከማድረግ አንስቶ እስከ የአካል ጉዳተኝነትን ጉዳይ በመደበኛው የትምህርት ስርአት ውስጥም እንደ አንድ የትምህርት ዘርፍ አድርጎ በማካተትና በማሰልጠን ባለሙያዎቹ ስለራሱ ስለ አካል ጉዳተኝነትም ያላቸውን ግንዛቤ እና ለአካል ጉዳተኞች ሊያደርጉት ተገቢ የሆነ ክብካቤ እና አያያዝ እንዲረዱ ማድረግ የሚያስፈልግ መሆኑን ነው።

ከዚህም ባሻገር፣ የሕክምና ባለሙያዎች የሚተዳደሩባቸውን የስነ-ምግባር ደንቦች ከአካል ጉዳተኞች መብትና ጥቅም አኳያ ቃኝቶ አስፈላጊውን ሁሉ ማሻሻያ ማድረግ ያስፈልጋል።

Health care education on disability should include a range of topics including clinical information, communication strategies and an introduction to a human rights approach to disability. Training beyond clinical information is important as explained in this article:

Doctors and other health professionals who encounter disabled people in their professional practice should be aware not only of the causes, consequences, and treatment of disabling health conditions, but also of the incorrect assumptions about disability that result from stigmatized views about people with

disabilities that are common within society… it is important for professionals to understand not just disease, but also the experience of living with disability.

### 3.6. ወሳኝ የማኅበራዊ ኩነቶች፣ ጤና እና የአካል ጉዳተኞች መብቶች

ከላይ በተደጋጋሚ እንደተገለጸው፣ የጤና መብት ማለት ሰዎች ሲታመሙ ሕክምና ማግኘት ብቻ ሳይሆን፣ ወሳኝ የሆኑ እና በጤና አጠባበቅ ላይ ቀጥተኛ የሆነ ተጽእኖ ያላቸው እንደ የንጹህ ውሃ እና የጽዳት ግብአቶች አቅርቦት፣ በቂ እና ተመጣጣኝ የሆነ ምግብ፣ የጤናማ እና ደህንነቱ የተጠበቀ የስራና አካባቢያዊ ሁናቴ፣ የስነ-ተዋልዶ እና ስነ-ጾታን ጨምሮ ጤና ነክ መረጃና የግንኙነት ስልቶች፣ መኖርንም ጭምር የሚያካትት ጥቅል ጽንሰ-ሀሳብ ነው።

እነዚህ ከላይ የተጠቀሱ የጤና ወሳኝ ግብአቶች በበኩላቸው በሌሎች ወሳኝ በሆኑ የማኅበረ-ኢኮኖሚ ዘርፎች ማለትም በስነ-ብእል/ኢኮኖሚያዊ (economics) የማኅበራዊ ፖሊሲ እና ፖሊቲካ አውድ ወሳኝ ኃይላት የሚቀረጹ ናቸው። በመሆኑም የአካል ጉዳተኞች የጤና መብት አረዳድ በአንቀጽ 24 ስር ከተደነገገው የትምህርት መብት፣ በአንቀጽ 27 ስር ከተደነገገው የስራ መብት ጋራ ተጣጥሞ መሄዱን ማረጋገጥ የግድ ይላል።

እነዚህ ከላይ የተጠቀሱ መብቶች የአካል ጉዳተኞችን ሁለንተናዊ የእውቀት፣ የግንዛቤ እና አረዳድ ከፍ ከማድረግ አንስቶ የኢኮኖሚ አቅማቸውን የሚያዳብሩ ወሳኝ የሰብአዊ መብቶች ክፍል ስለሆኑ ሳይነጣጠሉና ሳይሸራረፉ ከጤና መብት ጋራ መሳ ለመሳ ሊሄዱ ይገባቸዋል።

## ክፍል 4 የኢትዮጵያ ሕጎች ከአካል ጉዳተኞች የጤና መብት አኳያ

### 4.1. የጤና መብት በአካል ጉዳተኞች ስምምነት ውስጥ ያለው ይዘት እና የኢትዮጵያ ሕጎች

ከስምምነቱ አንቀጽ 25 ይዘትና አገላለጽ ለመረዳት የሚቻለው ነጥብ፣ "አካል ጉዳተኞች ምንም ዓይነት ልዩነት ሳይደረግባቸው ሊደረስበት በሚችለው ከፍተኛ የጤና ደረጃ ተጠቃሚ የመሆን መብት" ያላቸው መሆኑን ሲሆን፤ ለዚህ በጠቅላላ አገላለጽ ደረጃ ለተገለጸው መብት ተግባራዊነት ዋና ዋና አመላካች ነጥቦች ተብለው የሚወሰዱት ደግሞ፤

- በጠቅላላው የጤና አገልግሎት አሰጣጥ ውስጥ እንደማንኛውም የኅብረተሰብ ክፍል በዋነኛውም ሆነ በልዩ መልኩ በሚሰናዳ አገልግሎት እኩል ተጠቃሚ የሚሆኑበት (Equal access to mainstream and specific services within general health services) መኖሩ፤
- አካታች የሆነ የጤና መድህን ስርአት (Inclusive health Insurance) መኖሩ፤
- በመረጃ ላይ የተመሰረተ እና ነጻ ፈቃድ አሰጣጥ (Free and informed consent) መኖር የሚሉትን ያካትታል።

በዚህም መሰረት የአንድን አገር የሕግ ስርአት በተለይም የአካል ጉዳተኞችን የጤና መብት የሚመለከቱ ፖሊሲዎች፣ ሕግጋት፣ ስትራቴጂዎች፣ መርሀ-ግብሮች እና የጤናው ዘርፍ መራሄ-ሀሳቦች (guidelines) ሲቃኙ እነዚህን መሰረታዊ አመላካች ነጥቦች ታሳቢ በማድረግ መሆን ይገባዋል።

በመሆኑም እስከ አሁን ድረስ በኢትዮጵያ የሕግ ስርአት ውስጥ በቀጥታ የአካል ጉዳተኞችን የጤና መብት የሚመለከት መደበኛ ሕግም ሆነ ብሔራዊ ፖሊሲ ወጥቶ ስለመገኘቱ መረጃ የሌለ ሲሆን የሕጎች ሁሉ የበላይ የሆነው የኢፌድሪ ሕገ-መንግሥት በአንቀጽ 41(4) ስር እና በአንቀጽ 90 ስር የጤና መብትን ጨምሮ በኤኮኖሚ፣ ማኅበራዊና የባህል መብቶች አንጻር መንግስት ያለበትን ግዴታ ይገልጻል። በዚህ ድንጋጌ መሰረት መንግስት እያደገ በሚሄድ መጠን ለትምህርት፣ ለማኅበረሰብ ጤና እንዲሁም ለሌሎች የማኅበራዊ ዘርፍ አገልግሎቶች አስፈላጊውን ሀብት መመደብ አለበት። እንዲሁም ደግሞ የዚሁ ሕገ-መንግሥት አንቀጽ 90 (1) በአገሪቱ የሚወጡ ፖሊሲዎች የአገሪቱ የኤኮኖሚ አቅም በሚፈቅድ መጠን የሕዝብ ጤና፣ ትምህርት፣ የንጹህ ውሃ፣ ምግብ፣ የመኖሪያ ቤት እና ማኅበራዊ ዋስትና ተደራሽነትን ባማከለ አኳኋን ሊቀረጹ የሚገባ መሆኑን ያመለክታል።

ከላይ ከተገለጹት የሕገ-መንግሥቱ አናቅጽ ይዘት ለመረዳት የሚቻለው፣ ሕገ-መንግስታችን በቀጥታ የአካል ጉዳተኞችን የጤና መብት በተመለከተ የሚለው ነገር እንደሌለ ነው። ይሁን እንጂ በዚሁ ሕገ-መንግሥት አንቀጽ 9(4) መሰረት ኢትዮጵያ ያጸደቀቻቸው ዓለም-አቀፍ ስምምነቶች የአገሪቱ ሕግ አካል እንደሆኑ የሚቆጠሩ ስለሆነ እና የአካል ጉዳተኞች መብቶች ስምምነትን ኢትዮጵያ በአዋጅ ቁጥር 676/2002 ዓ.ም አጽድቃ የሕግስርአቷ አካል ስላደረገችው እንዲሁም ደግሞ በአንቀጽ 13(2) መሰረት በዚሁ ሕገ-መንግሥት ውስጥ የተዘረዘሩት ሰብአዊ መብቶችን የሚመለከቱት ድንጋጌዎች ኢትዮጵያ ካጸደቀቻቸው ዓለም-አቀፍ ስምምነቶች ይዘት አኳያ ተጣጥሞ መተርጎም የሚገባቸው መሆኑን የሚገልጽ ስለሆነ፣ መንግስት እና የሚመለከታቸው አካላት፣ በዓለም-አቀፉ የአካል ጉዳተኞች መብቶች ስምምነት አንቀጽ 25 ስር የተደነገገው የጤና መብት ይዘት ገቢራዊ የሚሆንበትን እርምጃ የመውሰድ ግዴታ አለባቸው።

ከዚህ ጥቂት ለየት በሚል አኳኋን፣ ከኢፌድሪ ሕገ-መንግሥት መውጣት በፊት በሽግግሩ ወቅት ወጥቶ ተግባራዊ ሲደረግ የቆየው የጤና ፖሊሲ፣ የፖሊሲውን አጠቃላይ አቅጣጫ በሚያመለከተው ክፍሉ፣ በተራ ቁጥር 3ስር፣ ባለው ውሱን ሀብትና አቅም ለሁሉም የኅብረተሰቡ ክፍል ፍትሐዊነትና ተቀባይነት ባለው መንገድ የጤና አገልግሎት የሚያደርስ ሥርዓት መዘርጋትና ማስፋፋት የሚል አቅጣጫ እንዳለው ያመለክታል። ከዚህም ባሻገር የጤናው ዘርፍ ለሁሉም ተደራሽ እንዲሆን ያሰበ መሆኑን በተራ ቁጥር 6 ስር የጤና ክብካቤ ዘርፉ ለሁሉም የኅብረተሰብ ክፍል ተደራሽ እና ምቹ መሆኑን ማረጋገጥ (Assurance of accessibility of health care for all segments of the population) በማለት ይገልጻል። እነዚህን ጠቅላላ ታሳቢዎች ከግምት በማስገባት የፖሊሲ ታሳቢዎችን እውን ለማድረግ ሊከተላቸው ካሰባቸው ጠቅላላ ስትራቴጂዎች (general strategies) መካከል የማኅበረሰብ-አቀፍ የአእምሮና አካል ጉዳተኞችን ለመንከባከብ የሚያስችሉ መአከላትን ማልማት (Participating in the development of community-based facilities for the care of the physically and mentally disabled, the abandoned, street children and the aged) የሚለው ይገኝበታል።

የዚህን ፖሊሲ አቀራረጽም ሆነ አገላለጽ በጥልቀት ስንመለከተው አካል ጉዳተኞች የሚለውን ጽንሰ-ሀሳብ በሚገባ ያልተገነዘበ ይመስላል። ከዚህም ሌላ በዋናው እና ለአጠቃላዩ ማኅበረሰብ አገልግሎት በሚሰጡ የጤና ተቋማት ውስጥ ስለሚኖረው አገልግሎትና አገልግሎቶቹን ለአካል ጉዳተኞች ተደራሽ ለማድረግ ስለሚያስፈልጉት የተደራሽነትና ምቹነት መርሆ በሚገባ በዝርዝር አልገለጸም። ይህ ደግሞ በስትራቴጂም ሆነ በዝርዝር ሕግጋት ደረጃ አስገዳጅ የሆኑ ድንጋጌዎችን አውጥቶ መብቶቹን ገቢራዊ ለማድረግ እንቅፋት ይሆናል።

ለዚህ ጽሁፍ ዓላማ ታሳቢ ከተደረጉ ሕግጋት መካከል በተለይም ደግሞ የአካል ጉዳተኞችን የጤና መብት በተለይ እና በአጠቃላይ የጤናውን ሴክተር ሕግጋት፣ ማለትም አዋጆች፣ ደንቦች፣ መመሪያዎች እና መራሄ-ሀሳቦች (guidelines) ይዘት ስንመለከት በግልጽ የአካል ጉዳተኞችን የጤና መብት ታሳቢ በማድረግ ቀጥተኛ ተፈጻሚነት ያላቸው ድንጋጌዎችን ይዘው አናገኝም። ከጉዳዩ ጋራ ተገናኝነት ያለው ሕግ በቅርቡ በረቂቅ ደረጃ ላይ የሚገኘው የአካል ጉዳተኞች መብት ረቂቅ አዋጅ ሲሆን፤ በዚህ አዋጅ ውስጥ ከአንቀጽ 32 እስከ 40 ድረስ ያሉት ድንጋጌዎች የጤና ጉዳይን የሚመለከቱ ናቸው። በአንቀጽ 32 (1) መሰረት አካል ጉዳተኞች ምንም ዓይነት ልዩነት ሣይደረግባቸው ሊደረስበት የሚችለው ከፍተኛ የጤና ደረጃ ተጠቃሚ የመሆን መብት አላቸው በማለት ከላይ በተጠቀሰው ዓለም-አቀፍ ስምምነት ዓይነት ግልጽ ድንጋጌ ይዞ እናገኘዋለን።

ረቂቅ አዋጁ በዚሁ አንቀጽ ንኡስ ቁጥር 2 ስር፣ የጤና ሚኒስቴር አካል ጉዳተኞች የመልሶ ማቋቋም እና የስነ-ተዋልዶ ጤናን ጨምሮ የተሟላ እና ደረጃውን የጠበቀ የጤና አገልግሎት እንዲያገኙ ለማስቻል ለአካል ጉዳተኞች ምቹ የሆኑ የጤና ማዕከላትን ያደራጃል፣ በቁሣቁስ እና በሰለጠነ ሰው ያሟላል.... በማለት የሚደነግግ ሲሆን የዚህ ድንጋጌ “ለአካል ጉዳተኞች ምቹ የሆኑ የጤና ማዕከላትን ያደራጃል፣” የሚለው አገላለጽ ልዩ የሆኑ አካል ጉዳተኞች ብቻ የሚጠቀሙባቸው መአከላት የሚል ትርጉም የሚያሰጠው የሚመስል ስለሆነ ማስተካከያ ያስፈልገዋል። እንደሚታወቀው ከላይ የተገለጹት ዓለም-አቀፍ ሕግጋት በዋነኛ የጤና አገልግሎት መስጫ መአከላት ውስጥም የሚሰጠውን የሕክምና አገልግሎት ለአካል ጉዳተኞች ተደራሽና ምቹ ማድረግ እንደሚገባና ልዩ የሆኑ መአከላት በተለየ ሁናቴ ያውም ደግሞ በዋና የጤና መአከላት ውስጥ ሊዘጋጅና ሁሉም የጤናው ዘርፍ አገልግሎቶች የአካል ጉዳተኞችን ሰብአዊ መብቶች ታሳቢ ባደረገ አኳኋን አካታች ሆኖ

መቀረጽ እንደሚገባው የሚደነግጉ ሲሆን ይህ ደግሞ የአካል ጉዳተኞችን የማኅበረሰባዊ ተካታችነት ከግምት የሚያስገባ በመሆኑ በተለይም ስለ አካል ጉዳተኝነት ያለው ግንዛቤ የደረሰበትን ደረጃ የዋጀ ስለሆነ፣ እንዳለ መቀበል ያስፈልጋል።

ከዚህ በተረፈ በዚህ ረቂቅ አዋጅ ውስጥ የተጠቀሱትን ድንጋጌዎች ስንመለከት በተለይ ደግሞ በመረጃ ላይ የተመሰረተ ነጻ ፈቃድ የሚለውን መሰረታዊ የአካል ጉዳተኞች የጤና መብት ጥራት አመላካች መስፈርት ከግንዛቤ ያስገባ ሆኖ አይታይም።

እንዲህ ያለው አመላካች ነጥብ በተለይም ደግሞ ከአእምሮና ከስነ-አእምሮ እክል ጋራ የተገናኙ አካል ጉዳተኞች የሚደርስባቸውን ሕክምና ነክ መጉላላትና መድልኦ ታሳቢ ያላደረገና የመብቱን አጠባበቅም ምሉእ እንዳይሆን ያደርገዋል። ከዚሁ ነጥብ ጋራ በተያያዘ፣ የሕክምና ባለሙያዎች የሙያ ስነ-ምግባር መተዳደሪያ ደንብ እንዲህ ያለውን የአካል ጉዳተኞች በመረጃ ላይ የተመሰረተና ነጻ የሆነ ፈቃድ አሰጣጥን የሚመለከት ግልጽ ድንጋጌ ይዞ መገኘት የሚገባው መሆኑን በሚያመላክት በረቂቅ ሕጉ ላይ ማካተት ያስፈልጋል። ምክንያቱም የአካል ጉዳተኞች መብቶች ስምምነት በአንቀጽ 25 ስር ከገለጻቸው መሰረታዊ የመብቱ ይዘቶች መካከል አንዱ በዚሁ አንቀጽ ፊደል ተራ (መ) ስር የተደነገገውና "ነፃ የሆነና በዕውቀት ላይ የተመሰረተ ፈቃድን ጨምሮ" ለመንግስትና ለግል የጤና እንክብካቤ መስጫ ተቋማት በሚሰጥ ስልጠናና በሚደነገግ "የሙያ ሥነ ምግባር ደረጃ" አማካኝነት ስለአካል ጉዳተኞች ሰብአዊ መብቶች ከበሬታ፣ የግል ነፃነትና ልዩ ፍላጎቶች ያላቸውን ግንዛቤ በማሻሻል የጤና ባለሙያዎች ለአካል ጉዳተኞች ከሌሎች ጋር አንድ አይነት የሆነና ጥራቱን የጠበቀ የጤና አገልግሎት እንዲሰጡ ማድረግ የሚለው የሚገኝበት በመሆኑ እና የጤና ባለሙያዎች የአካል ጉዳተኞችን መብቶች ታሳቢ ባደረገ መልኩ በሙያ ስነ-ምግባር መተዳደሪያ ደንቦቻቸው ውስጥ መደንገጉ ዘርፉ ለአካል ጉዳተኞች መብቶች መከበር ሊደርስበት የሚያስበውን ደረጃ እውን ለማድረግ ይረዳል። ከዚህም ባሻገር ከመብቱ ያለመከበር ጋራ በተያያዘ የሚቀርቡ አቤቱታዎችንም ለማስተናገድ ግልጽ መስፈርት ሆኖ ሊያገለግል ይችላል።

ሌላኛው ጉዳይ የጤና ባለሙያዎች በሕክምና ትምህርታቸው ወቅትም ሆነ በስራ ላይ ስልጠና የአካል ጉዳተኞችን ሰብአዊ መብቶች አከባበርና ስለ አካል ጉዳተኝነት ምንነትም ሆነ ሊደረግ ስለሚገባው ክብካቤ ሁሉ በግልጽ ሊያስገነዝብ የሚችል ተግባራዊ እና ተከታታይነት ያለው ስልጠና እና በሕክምና ትምህርት እና ስልጠና አሰጣጥ ስርአት ውስጥም አስገዳጅ ቅድመ ሁናቴ አድርጎ ማካተት ያስፈልጋል።

### 4.2. መወሰድ ስለሚገባቸው እርምጃዎች

የጤና መብት ገቢራዊነት የሕክምና ዘርፉን ብቻ የሚመለከትና በአንድ ወይም ሁለት አካላት ብቻ እውን ሊሆን የማይችል በመሆኑ ምክንያት፣ ሊወሰዱ የሚገባቸው እርምጃዎችም ቢሆን የሁሉንም አካላት የጥምረት ስራ የሚፈልግ ነው። ለምሳሌ ያክልም ከጤና ሚንስቴር ባሻገር የሌሎቹን የማኅበራዊ ዘርፎች ተግባራዊ እንቅስቃሴና የጣምራ ስራ ማረጋገጥና የአካል ጉዳተኞች ማህበራት ተሳትፎ የግድ ይላል። በዚህ መሰረትም፤

- በመጀመሪያ በዘርፉ ተግባራዊ የሚሆኑ የፖሊሲ ሰነዶችን ጨምሮ ሌሎችንም ሕግጋት ፈትሾ ያላቸውን ተፈጻሚነት እና ምቹነት ማረጋገጥ፤

- በቀጣይም በተለይም የአካል ጉዳተኞች የጤና መብት ከሌሎቹ የማኅበረሰቡ አካላት ጋራ እኩል በሆነ ደረጃ እውን የሚሆንበትን መንገድ መፈለግ፤ በልዩ ሁናቴም የብሔራዊ የተደራሽነትና ምቹነት ፖሊሲ እንዲኖርና የሚወጡትም ሕግጋት ወይም የሚወሰዱት እርምጃዎች ይህንን ፖሊሲ ታሳቢ ያደረገ መሆኑን ማረጋገጥ፤
- በተለይም የሕክምና ቁሳቁሶች ግዢም ሆነ የምርት ሂደቱ ሲከናወን የአካል ጉዳተኞችን መብቶች በተለይም የመረጃ ማግኘት መብታቸውን ከግንዛቤ ያስገባና በላዩም ለአካል ጉዳተኞች በሚገባ መልኩ በግልጽ በሚታዩና ሊነበቡ በሚችሉ እንደ ብሬል እና ሌሎችም መንገዶች የመድሀኒቶቹን ስም፣ ኬሚካላዊ ይዘት እና ሌሎችንም መሰረታዊ ይዘቶቻቸውን በሚገልጽ መንገድ መዘጋጀታቸውንና ወደ አገር ሲገቡም በሚመለከተው አካል በኩል እንደ አንድ የደረጃ መለኪያ ሆነው መካተታቸውን ማረጋገጥ ያስፈልጋል፤
- ከዚህ ጋራ በተያያዘ የኢትዮጵያ የምግብና መድኃኒት አስተዳደር አዋጅ ቁጥር 1112/2011 አንቀጽ 53 (3) በሀገሪቱ መሰረታዊ የመድኃኒት ዝርዝር ውስጥ የተካተተ ወይም በብዛት የሚሰራጭ መድኃኒት በአባሪነት የሚካተት ገላጭ ጽሁፍ በአማርኛ እና በእንግሊዝኛ ቋንቋ መጻፍ ያለበት ሆኖ ምርቱ በአንድ ክልል ውስጥ ብቻ የሚከፋፈል ከሆነ ገላጭ ጽሑፉ ቢያንስ በእንግሊዝኛና በክልሉ የሥራ ቋንቋ ይሆናል ከማለቱ ውጪ ለአካል ዱዳተኞች ተደራሽና ምቹ በሆነ መንገድ ወይም ስልት በብሬል ወይም በሌላ ተነባቢ በሆነ ጽሁፍ ወይም ምልክት መዘጋጀት ያለበት መሆኑን በማካተት አይደነግግም። በዚህም ምክንያት የአካል ጉዳተኞችን የጤና ነክ መረጃ ማግኘትና የእኩል ተጠቃሚነት መርህ የማያከብር በመሆኑ በዚሁ መሰረት አዋጁ እንዲሻሻል ወይም ደግሞ በመመሪያ ደረጃም ካለ፣ በአካል ጉዳተኞች መብት አዋጅ ውስጥ በአዋጅ ደረጃ እንዲካተት ማድረግ ያስፈልጋል፤
- የሕክምና መአከላት ግንባታም ሆነ የሕክምና መስጫ ቁሳቁሶችና አገልግሎቶቹ እንዲሁም ደግሞ መድኃኒቶች የአካል ጉዳተኞችን መብቶችና ልዩ ፍላጎቶች ታሳቢ ያደረጉ መሆናቸውን የሚከታተል ራሱን የቻለ አካል ሊኖር ይገባል፤
- የሆስፒታሎች ግንባታ ብቻ ሳይሆን የሌሎቹ የሕክምና መስጫ መአከላት በተለይም ደግሞ በገጠር አካባቢ የሚገኙ እንደ የጤና ኤክስቴንሽን መአከላት ከአካል ጉዳተኞች መብት በተለይም የመአከላቱ የቁስ-አካላዊ ተደራሽነት መርሆ ጋር ተሰናስሎ ሊታይና በመጀመሪያ ግንባታው ሲካሄድ በሁሉን-አቀፍ ንድፍ (universal design) መለኪያ ወይም በምክንያታዊ ማሻሻያ ወይም (reasonable accommodation) መስፈርት ደረጃ ሊቃኝ እና ማስተካከያ ሊደረግበት ይገባል።